በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

<u>ማውጫ</u>

**መዝሙር ዘዘወትር ዘድንግል ማርያም....8**
1. ዕዳ አለብን....8
2. እመቤታችን....8
3. ሰላም ላንቺ ይሁን....9
4. አዛኝቷ እመቤት....9
5. የጠሩሽ....10
6. እንዘ ተሐቅፊዮ....11
7. አንቺ የወይን ሐረግ....11
8. በእንተ ማርያም....11
9. ሰላም ለኪ....11
10. ሰላም ለኪ ለኖኅ ሐመሩ....12
11. ትርሲተ ወልድ....12
12. ምስለ ሚካኤል....12
13. ምንተኑ አአስየኪ....13
14. ንዒ....13
15. ፀምር ፀዓዳ....13
16. ወዳጄ ሆይ....14
17. ምስጋና ለስምሽ....14
18. ትበርህ ማርያም....15
19. እናታችን ጽዮን....15
20. አዳም ወሠናይት....15
21. ብኪ ድኅነ ዓለም....16
22. ፍስሐ ወሰላም....16
23. እዘኝልን....16
24. ሰአሊ ለነ....17
25. ንዒ ሀቤነ....17
26. ፍቅርኪ መፅሐፍ....17

27. በአልባሰ ወርቅ ........ 18
28. ሰአሊ ለነ ቅድስት ........ 18
29. ሐዋርያት ይብልዋ ........ 18

መዝሙር በእንተ ልደታ ለድንግል ማርያም ........ 19
30. ተፈፀመ ሐና በወለትኪ ........ 19

መዝሙር በእንተ ስደታ ለድንግል ማርያም ........ 19
31. አስምኪ ቦቱ ........ 19
32. ድንግል መከራሽን ........ 19
33. የጻድቃን እመቤት ........ 20
34. ምዕረ በዘባንኪ ........ 20

መዝሙር በእንተ ብስራት ........ 20
35. ወእንዘ ትፈትል ........ 20
36. አመ ኀደረ ........ 21
37. አስተርአያ ........ 21
38. ገብርኤል አብሠራ ........ 21
39. ለድንግል ገብርኤል አብሠራ ........ 21
40. መልአክ በሰላም ........ 22

መዝሙር በእንተ ዕርገታ ለድንግል ማርያም ........ 22
41. ዕርገታ ተሰምዓ ........ 22
42. ወላዲተ ቃል ........ 22

መዝሙር ዘዘወትር ........ 23
43. በስመ ሥላሴ ........ 23
44. የሥላሴን መንበር ........ 23
45. ቅዱስ ቅዱስ ........ 23
46. ስብሐት ለሥላሴ ........ 24

47. እናመስግነው ........................................................................................24
48. መዓትህን አርቅ ....................................................................................24
49. ወመኑ መሐሪ ......................................................................................24
50. ኦ አንትሙ ...........................................................................................25
51. ሃሌ ሉያ ..............................................................................................25
52. ለአምላካችን እንዘምር ..........................................................................25
53. ኵሉ ከንቱ ............................................................................................26
54. እናመስግነው ........................................................................................26
55. ሁላችን እንፀልይ ..................................................................................27
56. ኃይሉን ያለብሰኛል ..............................................................................27
57. የቀደመ በደላችንን ................................................................................28
58. ዘይክል ኵሎ ........................................................................................28
59. ወዘምሩ ለስሙ ......................................................................................28
60. ሁላችን እናቅርብ ..................................................................................29
61. የሕይወት እንጀራ ..................................................................................29
62. ማን እንደ እርሱ ..................................................................................30
63. መንግሥቱ ዘለዓለም ..............................................................................30
64. ለአምላክ ተቀኙ ....................................................................................30
65. ከሕግ እንዳንወጣ ..................................................................................31
66. ተነሱ እንዘምር ......................................................................................31
67. ኖላዊ ትጉህ ..........................................................................................32
68. አትልፊ በከንቱ ......................................................................................32
69. መንክር እግዚአብሔር ..............................................................................33
70. ይትባረክ እግዚአብሔር ............................................................................33
71. እግዚአብሔር ዐቢይ ..............................................................................33
72. ወሥኑስ ................................................................................................33
73. ዘመንበሩ ዓቢይ ......................................................................................33

መዝሙር በእንተ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ....................................34
74. ሰማይና መሬት ......................................................................................34

75. አምላክ ሰው ለመሆን ........ 34
76. ገብርኤል አወፈየኒ ........ 34
77. አንፈርዓፁ ሰብአሰገል ........ 35
78. ዘነቢያት ሰበክዎ ........ 35
79. አንፈርዓፁ ........ 35
80. በኮከብ መጽኡ ........ 35
81. መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ ........ 35
82. የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው ........ 36
83. መጽአ ወልድ ........ 36
84. ዘድንግል መናሥግተ ........ 36

መዝሙር በእንተ ጥምቀቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ........ 37
85. ኢየሱስ ሖረ ........ 37
86. መድኃኒነ ........ 37
87. ይእዜኒ ........ 37
88. መጽዐ ቃል ........ 37
89. አስተርአየ ........ 37
90. ነአምን ........ 37

መዝሙር በእንተ በዓለ ቃና ዘገሊላ ........ 38
91. እንዘ ይገብር ........ 38
92. የማይሞተው ሞተ ........ 38
93. ወፀሐፈ ጲላጦስ ........ 39
94. ምድረ ቀራንዮ ........ 39
95. ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ........ 39

መዝሙር በእንተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ........ 40
96. ምድር ፀዳች ........ 40
97. ክርስቶስ ተንስአ ........ 41
98. እንዘምር ሁላችን ........ 41

99. በትንሣኤከ......41
100. ሰላም ሰላም......42
101. የትንሣኤው ብርሃን......42

መዝሙር በእንተ ዕርገቱ ለእግዚእነ......42
102. ሞያ ለሞት......42
103. ይቤሎሙ ኢየሱስ......43
104. ንግበር በዓለ......43

መዝሙር በእንተ በዓለ ደብረ ታቦር......43
105. የታቦር ተራራ......43
106. አሐደ ለከ......43

መዝሙር በእንተ ቅዱሳን መላእክት......44
107. ሚካኤል ብሂል......44
108. ውእቱ ሚካኤል......44
109. አንስዕ ኃይለከ......44
110. ሚካኤል......44
111. ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ......45
112. ሠለስቱ ደቂቅን......46
113. እም እቶነ እሳት......46
114. ንቁም በበህላዌነ......47
115. ከመትባርከነ......47
116. ስዩም በዲበ ኃይላት......47
117. ብቃት ስለሌለህ......48

መዝሙር በእንተ ቅዱሳን......48
118. ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ......48
119. ለምኑልን......49
120. ወጽአ እምድረ ካራን......50

121. በጾም ወበጸሎት ...... 50
122. ካሕን ወነቢይ ...... 50
123. ሐዋርያት ተባበሩ ...... 50
124. ንዋይ ኅሩይ ...... 51
125. ኦ ፍጡነ ረድኤት ...... 51
126. ደም ወማይ ...... 52
127. ዮም ተጽህፈ ...... 53
128. አርሴማ ቅድስት ...... 53
129. ጊዜ እረፍታ ለሶልያና ...... 53
130. ሕፃን ወእሙ ...... 53
131. አቁረርከ ቂርቆስ ...... 53
132. ነፍስየ ትባርኮሙ ...... 54
133. ዜናኩ ጽድቀከ ...... 54
134. አልቦ እምቅድሜሁ ...... 54
135. ብፁዕ ውእቱ ...... 54

መዝሙር በእንተ ጾም ...... 55
136. እንፁም እንፀልይ ...... 55
137. ሙሴኒ ጾመ ...... 55

መዝሙረ ንስሐ ...... 55
138. ሥጋውና ደሙን ...... 55
139. ስማኝ አምላኬ ...... 56
140. በከሃሊነቱ ...... 56

መዝሙር በእንተ መስቀሉ ለእግዚእነ ...... 57
141. መስቀልከ ...... 57
142. በመስቀልከ ...... 57
143. መድኃኒት ...... 57

መዝሙር በእንተ ቤተ ክርስቲያን....57
144. የቅዱሳን በዓት ....57
145. ተቀደሲ....58
146. እምርጉቅሰ....58
147. አይ ይእቲ ....58
148. አመ ትትሐነጽ ....58
149. ቤተክርስቲያን አሐቲ ....59

መዝሙር በእንተ ዓውደ ዓመት ....59
150. ዓውደ ዓመት መጽአ....59
151. ዓውደ ዓመት ለባርኮ....59
152. አመ ከመ ዮም ....59
153. ያብጽሐነ....59
154. ርዕሰ ዓውደ ዓመተ ....60

መዝሙር በእንተ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ....60
155. የክርስቲያን ደሴት ....60
156. ኢኮነ ነግደ....60
157. ሰላም ለኪ....61

መዝሙር በእንተ ጉባዔ....61
158. ናሁ ሠናይ....61
159. ባርክ ለዝ ጉባዔ....61

## <u>መዝሙር ዘዘወትር ዘድንግል ማርያም</u>

1. **<u>*ዕዳ አለብን*</u>**
**/ኪነጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.2/**

የእመቤታችን አማላጅነቷን
ክብሯን የቀነስን ያዋረድን
<u>ዕዳ አለብን</u>/2/ ከፈጣሪያችን/2/
የተሰጣት ሙሉ ሥልጣን
ክብርን ያገኘች በቃል ኪዳን
ስሟን የጠራ እንደሚድን
በመጽሐፍ ሲነገረን
አዝ ...
ቤዛዊተ ኩሉ የተባለች
በእነ ቅዱስ ኤፍሬም የተመሰገነች
በእነ አባ ጊዮርጊስ ውዳሴን ያገኘች
በመናፍቃን ዘንድ ምነው ተዘነጋች
አዝ ...
ከሴቶች ሁሉ ልዩ ናት እያልን
በሁለቱም ወገን በፍፁም ድንግል
የብርሃን እናቱ ማርያም ስትባል
በደካሞች ዘንድ እንዴት ትቃለል
አዝ ...
ቃና ዘገሊላ ከልጇ ጋር ሳለች
ከሠርግ ቤትገብታ ድንግል አማልዳለች
እንኳንስ እመአምላክ ቤዛዊተ ኩሉ
ጻድቃን ሰማዕታት በእውነት ያማልዳሉ፡፡
አዝ ...

2. **<u>እመቤታችን</u>**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ.መ. - ቁ.1/**
እመቤታችን ሳንቺ እናቀርባለን ምስጋና

አንቺ የወለድሽው ክርስቶስ የዓለም መድሃኒት ሆኗልና
ህፃናትም ስላወቁ ደግነትሽን በሙሉ
ወደ አንቺ ሁል ጊዜ ይማልላሉ
ከፈጣሪሽ አማልጂን እያሉ
ወጣቶችም ስላወቁ ደግነትሽን በሙሉ
ወደ አንቺ ሁል ጊዜ ይማልላሉ
ከፈጣሪሽ አማልጂን እያሉ

**3. ሰላም ላንቺ ይሁን**
**/ተምሮ ማስተማር - ቁ. 1/**

ሰላም ላንቺ ይሁን /3/ ማርያም ድንግል /2/
የሴቶች መመኪያ የሴቶች አክሊል /2/
የሴቶች መመኪያ የሴቶች /2/ የሴቶች አክሊል
ሰላም ላንቺ ይሁን /3/ የሁሉ እመቤት /2/
የኃጥአን ተስፋ የጻድቃን ሕይወት /2/
የኃጥአን ተስፋ የጻድቃን /2/ ሕይወት
ሰላም ላንቺ ይሁን /3/ የሁሉ ወዳጅ /2/
የጽድቅ መሰላል የዓለም አማላጅ /2/
የጽድቅ መሰላል የዓለም /2/ አማላጅ
ሰላም ለወለድሽው /3/ አምላካችንን /2/
ሰማይና ምድር የማይችሉትን /2/
ሰማይና ምድር የማይችሉት የማይችሉትን
ሰላም ለእመቤቴ /3/ አምላክን ለወለድሽ /2/
የሰማይ መላእክት የሚያመሰግኑሽ /2/
የሰማይ መላእክት /2/ የሚያመሰግኑሽ
ሰላም ለእመቤቴ /3/ አምላክ ለመረጠሽ /2/
ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ ነሽ /2/
ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ /2/ ነሽ

**4. አዛኝቷ እመቤት**
**/ዲ - ታደለፌጣ - ቁ.1/**

አዛኝቷ እመቤት አትርሺኝ
የፈጣሪዬ እናት አስታውሽኝ
በምሕረትሽ /3/ ተማለጅኝ

የመከራ ነፋስ አጠቃኝ
ሕይወቴ ዝላለች ደከመኝ
ከጥላሽ ስር /3/ አሳርፊኝ

አዛ...

ከጭንቀት ባሕር ውስጥ አድኚኝ
ፈጥኜ ሳልጠፋ አስጥይኝ
እመቤቴ /3/ ተመልከቺኝ

አዝ...

 አምላኬን ለማየት አልችልም
ኃጢአቴ ብዙነው አይሆንም
ካልደገፍሽኝ /3/ እኔ አልድንም

አዝ...

ድንግል እመቤቴ እባክሽ
ከፈጣሪ አስታርቂኝ ከልጅሽ
ያላንቺ ማን /2/ ያላንቺ ማን አለኝ አስታዋሽ

**5. የጠሩሽ**
**/ተምሮ ማስተማር ሰ/ት/ቤት - ቁ.1/**

የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው የዳኑብሽ
የበላዔ ሰብእ እመቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝቱ ማርያም ቅድስት /2/

በቃል ኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል
በምልጃሽም ጽድቅን አግኝተዋል
የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል /2/

አዝ . . .

የእሳት ባህርን በአንቺ ተሻግረዋል
የሰይጣንን ጾር በአንቺ ድል ነስተዋል
ለሰማያዊው ክብር በቅተዋል /2/

አዝ . . .

ነፍሳቸውም ጽድቅን አግኝታለች
ሕይወታቸውም በአንቺ ትድናለች
ድንግል ሆይ አትጣይኝ ስላለች /2/

አዝ . . .

እኔ በአንቺ እታመናለሁ
የአምላክ እናት አሳስቢ እላለሁ
በአማላጅነትሽ እድናለሁ /2/

አዝ . . .

እኛ በአንቺ እንታመናለን
የአምላክ እናት አሳስቢ እንላለን
በአማላጅነትሽ እንድናለን /2/

አዝ . . .

ምእመናንም በአንቺ ያምናሉ
የአምላክ እናት አሳስቢ ይላሉ
በአማላጅነትሽ ይድናሉ /2/

አዝ . . .

**6.** **<u>እንዘ ተሐቅፊዮ</u>**
**/ፋንቱ ወልዴ - ቁ.4/**

እንዘ ተሐቅፊዮ ለሕፃንኪ ድንግል/2/
ምስለ ሚካኤል/4/ ፍሱሕ ወገብርኤል/2/

<u>ትርጉም</u>:- ድንግል ሆይ ሕፃንሽን /ልጅሽን/
ታቅፊሽ ደስ ካለው ከሚካኤል እና
ደስታን ከሚያበስር ከገብርኤል ጋር ነይ።

የሚዘመርበት ወቅት: መስከረም 26 - ኅዳር 6(ዘመነ ጽጌ)

**7.** **<u>አንቺ የወይን ሐረግ</u>**
**/መሪ. ዮሐንስ ስመኝ - ቁ.1/**

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ/2/
<u>ምግብ ሆኖ</u> /2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለኛ ቤዛ/2/ ኧኸ

ባንቺ ሰማይነት የወጣው ፀሐይ/2/
<u>ብርሃን ነው</u> /2/ ለፃድቃን ስሙም አዶናይ/2/ ኧኸ
አዝ...
ፊደል ትመስያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ/2/
<u>ለመላእክት</u> /2/ የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ/2/ ኧኸ
አዝ...
የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኮከብ መገኛ/2/
በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለኛ/2/ ኧኸ
አዝ...

**8.** **<u>በእንተ ማርያም</u>**
**/ብዙአየሁ ተመስገን - ቁ.3/**

በእንተ ማርያም /2/ ወላዲትከ ወበእንተ ዮሐንስ ፍቁርከ /2/
ርድአነ አግዚኦ በኃይለ መስቀልከ /2/

<u>ትርጉም</u>:- ስለወለደችህ እናትህ ማርያምና ስለወዳጅህ ዮሐንስ
ብለህ አቤቱ በመስቀልህ ኃይል እርዳን

**9.** **<u>ሰላም ለኪ</u>**
**/መሪ. ብርሃኑ ውድነህ - ቁ.3/**

ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ
ማርያም እምነ ናስተበቁዓኪ
እምአርዌ ነዓዊ ተማኅፀነ ብኪ
በእንተ ሐና እምኪ
ወኢያቄም አቡኪ

ማኅበረነ ዮም ድንግል ባርኪ

ሰላም ለአንቺ ይሁን ስግደትም ለአንቺ ይሁን
ማርያም እናታችን የመለኮት ዙፋን
ከኃይለኛ አውሬ የምትጠብቂን
ስለቅድስት ሐና ብለሽ ስለኢያቄም ካህን
ማኅበራችንን ድንግል ባርኪልን

**10.** **<u>ሰላም ለኪ ለኖኅ ሐመሩ</u>**
**/ዲ/ን እንግዳወርቅ- ቁ.1/**

ሰላም ለኪ ለኖኅ ሐመሩ
ሰላም ለኪ ለአሮን በትሩ
ሰላም ለኪ ለቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ
ሰላም ለኪ ለጌድዮን ፀምሩ
ሰላም ለኪ ለሰሎሞንም መንበረ ክብሩ
ሰላም ለኪ ለፍሬ ስብሐት መዖሩ /2/
እመ እግዚአብሔር ፀባኦት ሰላም ለኪ
ሰላም ለኪ ሠረገላሁ ለአሚናዳብ
ሰላም ለኪ መና ያለብሽ ንጹሕ መሶብ
ሰላም ለኪ ያዕቆብ ያየሽ በሎዛ
ሰላም ለኪ የይስሐቅ መዓዛ
እንዘ ንሴፈዎ ለበረከትኪ ዘምስለ አምኃ ንሰግድ ለኪ
ሰላም ለኪ ኅብስተ መና ዘእስራኤል
ሰላም ለኪ የሰማዕታት ንጹሕ አክሊል
ሰላም ለኪ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና
ሰላም ለኪ የኤልያስ መና
እንዘ ንሴፈዎ ለበረከትኪ ዘምስለ አምኃ ንሰግድ ለኪ

**11.** **<u>ትርሲተ ወልድ</u>**
**/ዲ/ን መገርሳ - ቁ.2/**
ትርሲተ ወልድ መለኮት ወፍቅር ኀደረ ላዕሌሃ ኀደረ/2/
ይቤላ ርግብየ ወይቤላ ሠናይትየ ማርያም ድንግል /2/

<u>ትርጉም</u>:- የወልድ ሽልማት፣ መለኮቱ፣ ፍቅሩም በእርሷ አደረ::
ወልድ መልካሚ ርግቤ ሆይ አላት ድንግል ማርያምን::
(በሰሎሞን አድሮ የተናገረ እርሱ ነውና::)
የሚዘመርበት ወቅት: ታኅሳስ 3

**12.** **<u>ምስለ ሚካኤል</u>**
ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንዒ ሠናይትየ ማርያም/2/
ንዒ ድንግል ንዒ/2/ ድንግል ምስለ ሚካኤል/2/ ኧኸ

ትርጉም:- መልካሚቱ ማርያም ድንግል ከሚካኤል ጋር ነይ::

የሚዘመርበት ወቅት: መስከረም 26 - ኅዳር 6(ዘመነ ጽጌ)

13. **ምንተኑ አአስየኪ**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

ምንተኑ አአስየኪ እሴተ
በእንተ ኵሉ ዘገበርኪ ሊተ /2/
የቅዱሳን ተስፋ የትንቢት ምዕራፍ
የስደተኞች ስንቅ የምሕረት ደጃፍ
የፍጥረት መመኪያ ምክንያተ ድኂን
ለእኔም ለመንገዴ ስለሆንሽኝ ብርሃን
አዝ . . .
የዓለም ኑሮ ማርኮኝ ልቤ ሲዋልል
በፈተናው ብዛት በሕይወት ስዝል
ለሥጋዬ ፈቃድ ከቶ ስላልተውሽኝ
ለነፍሴም ሰላምን ስላስገኘሽልኝ
አዝ . . .
በኃጢአት መጎስቆሌን ድካሜን ሳታዪ
በሐዘን በችግሬ ከእኔ ሳትለዪ
ከመከራ አዘቅት በአንቺ ስለወጣሁ
ለብዙ ውለታሽ ምን እከፍልሻለሁ
አዝ . . .

የአዝማቹ ትርጉም: ስላደረግሽልኝ ሁሉ
ምን እከፍልሻለሁ ማለት ነው::

14. **ንዒ**

ንዒ ርግብየ /4/
ትናዝዘኒ ኃዘነ ልብየ/4/

ትርጉም:- ርግቤ ሆይ (ድንግል ማርያም)
የልቤን ኃዘን ታረጋጊኝ ዘንድ ነይ

15. **ፀምር ፀዓዳ**

ፀምር ፀዓዳ መሶበ ወርቅ እንተ መና መሶበ ወርቅ/2/
በትረ አሮን እንተ ሠረፀት/2/ መሶበ ወርቅ/2/

ትርጉም:- ነጭ ጸምር /ባዘቶ/ መና ያለባት መሶበ
ወርቅ የለመለመች የአሮን በትር ድንግል ማርያም ናት::

16. **<u>ወዳጄ ሆይ</u>**
**/ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት - ቁ.2/**

ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ
የታተመች ፈሳሽ እንከን የሌለሽ
የተዘጋች መቅደስ ንጽሕት አዳራሽ
ሕዝቅኤል ያየሽ የምስራቋ በር
ማንም ያልገባባት ከአምላክ በስተቀር
የልዑል ማደሪያ አማናዊት መቅደስ
ስለንጽሕናሽ ምስጋናን እናድርስ
አዝ . . .
ሁለቱንም የሆንሽ እናትና ድንግል
ማኅደረ መለኮት ወላዲተ ቃል
ያለዘርአ ብዕሲ በኅቱም ድንግልና
አምላክን የወለድሽ ሐመልማለ ሲና
አዝ . . .
ምስራቀ ምስራቃት ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ
ጨረቃን የምትመስይ ፀሐይን የወለድሽ
የማለዳ ብርሃን ለዓይን የምታሳሺ
ጽዮን እናቴ ሆይ ከጎኔ አትሽሺ
አዝ . . .

17. **<u>ምስጋና ለስምሽ</u>**
**/ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት - ቁ.1/**

ምስጋና ለስምሽ ድንግል እመቤቴ
በአንቺ አማላጅነት ድኅነት በማግኘቴ
ቅዱሳን አባቶች ቀንም ከሌሊት
ለአንቺ ይቀኛሉ እንዲህ በማለት
ከሀገረ ብህንሳ ፍቅርሽ አስገድዶት
የአንቺ ንጽሕና ፍጹም አስደንቆት
አባ ሕርያቆስ ተሞልቶ በመንፈስ
ድንግል ሆይ አለ አንቺን ለማወደስ
አዝ . . .
ፋራን የተሰኘሽ የዕንባቆም ተራራ
በረከት የሞላሽ የገነት አዝመራ
ዕፀ ጳጦስ የተባልሽ የሙሴ ጽላት
የይስሐቅ መዓዛ የአብርሃም ደግነት
አዝ . . .
እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ
በቀኝ ትቆማለች አምራ ንግሥቲቱ
ባለገንዘቦችም አሕዛብ በሙሉ
ለክብርሽ ዝቅ ብለው ለአንቺ ይሰግዳሉ
አዝ . . .

ዓለም የዳነብሽ አንቺ የኖኅ መርከብ
ምስጋናሽ መብዛቱ እንደሰማይ ኮከብ
ዘወትር ሁልጊዜ ቢሰላ ቢወራ
ድንግል ሆይ አያልቅም የአንቺ ድንቅ ሥራ
አዝ . . .

**18. <u>ትበርህ ማርያም</u>**

ትበርህ ማርያም ፀሐይ ትበርህ/2/
ማርያም ፀሐይ/4/ ትበርህ ማርያም ፀሐይ /2/ ኧኸ

<u>ትርጉም</u>:- የብርሃን እናቱ ፀሐይ ማርያም
ከፀሐይ ይልቅ ታበራለች።

**19. <u>እናታችን ጽዮን</u>**

**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና
መጠጊያ ማረፊያ ጥላችን ነሽና
ከገነት ብንወጣ ማረፊያ ሆንሽን
የምሕረት ደመና ውኃ ሰጠሽን
የሕይወት እንጀራን አመጣሽልን
በአስራትም በአደራም ለአንቺ ተሰጠን
አዝ . . .
የኤልሳቤጥ አጽናኝ የጭንቅ ቀን ደራሽ
የኃጢአታችን ብዛት ዳገት ሳይሆንብሽ
ምሥራችን ደስታን ይዘሽልን መጣሽ
ማርያም ስንልሽ ደረስሽልን ፈጥነሽ
አዝ . . .
ውለታሽ ብዙ ነው ለልብ የማይጠፋ
ስምሽ መጽናኛ ነው አዝኖ ለተከፋ
በእንተ ማርያም ብሎ ለለመነ
የሰማይ የምድሩም ማንም አልጨከነ
አዝ . . .
በትራችን አንቺ ነሽ የምትደግፊን
ባሕረ እሳትን የምታሳልፊን
ጽርሐ ሥላሴ ነሽ ማኅደረ መለኮት
ሁልጊዜ አንጠግብሽም እንላለን ብጽዕት
አዝ . . .

**20. <u>አዳም ወሠናይት</u>**

አዳም ወሠናይት /4/
ማርያም/2/ አዳም ወሠናይት/4/ ኧኸ

ትርጉም:- ማርያም ያማረች መልካም ናት።
በኀልዮ (በሐሳብ) በነቢብ (በመናገር) በገቢር
(በመሥራት) ንጽሕት እንደሆነች ሲናገር ነው።

21. **ብኪ ድኅነ ዓለም**
ብኪ ድኅነ ዓለም/4/
ወበወልድኪ ኮነ ሰላም/4/ ኧኸ

ትርጉም:- ባንቺ ዓለም ዳነ በልጅሽም ሰላም ሆነ።

22. **ፍስሐ ወሰላም**
ፍስሐ ወሰላም የኀሉ ምስሌነ /2/
ድንግል ማርያም እምነ /4/ ኧኸ

ትርጉም:- ደስታና ሰላም ከእኛ ጋር ይሁን ድንግል
ማርያም እናታችን ናትና።

23. **እዘኝልን**
**/አዳነች አስፋው ቁ.2/**

እዘኝልን ድንግል የአምላክ መንበር
ዓለሙን በማየት ወድቀን እንዳንቀር /2/
በኃጢአት በበደል ከልጅሽ ለራቅን
በዝሙት በሀሜት ዛሬም ለወደቅን
በዲያብሎስ ተንኮል ለተተበተብን
በአማላጅነትሽ ዛሬም ተማፀኚ
ከኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረትን ለምኚ /2/
በንስሃ ታጥበን በፍቅሩ ተስበን
ከልጅሽ እግር ስር ለመቀመጥ አብቂን /2/

በፈፀምነው በደል ተፀፃች አድርጊን
መራራ እንባ እናፍስ ልብን መልሽልን /2/
ፈቃደ ሥጋና ፈቃደ ሰይጣን
ዓለም ተደርባ ስታስጨንቀን /3/
ሰላምን ተጠምተን ስንንከራተት
ድንግል ድረሽልን የአምላክ እናት /2/
እባክሽ አትለይን እስከመጨረሻው
እየቀረበ ነው የክርስቶስ መምጫው /2/
ድንግል ማርያም ሆይ እባክሽ አሳስቢ
ለጻድቃን አይደለም ለኃጥአን ብለሽ /2/

በቀኝ እንዲያቆመን በዳግም ምጽአቱ
ድንግል ለምኝልን ለአምላክ እናቱ
ድንግል ለምኝልን ለአምላክ ወላዲቱ
ቡሩካን ልጆቼ ብሎ እንዲቀበለን

ፍቅሩን ቸርነቱን አስቦ እንዲምረን /3/
ድንግል አደራሽን ስለኛ አሳስቢልን
በእርሱ መሠረት ላይ ክርስቶስ ያቁመን /2/

24. **ሰአሊ ለነ**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

ሰአሊ ለነ ማርያም ሰአሊ ለነ /2/
ወልድኪ ይምሐረነ ወመዋርስቲሁ ይረስየነ መድኃኒዓለም /2/

ለምኝልን ድንግል ማርያም ለምኝልን /2/
ልጅሽ ይቅር እንዲለን የመንግሥቱም ወራሾች እንዲያደርገን /2/

25. **ንዒ ሀቤነ**
**/መ/ል/ቅ/ማር/ስ/ት/ቤት ቁ.1/**

ንዒ ሀቤነ ኦ ድንግል
ምስለ ወልድኪ መድኃኒነ
ከመ ትባርኪ ላዕሌነ

ነይ ከአምላክሽ ጋር ከልጅሽ
ይቅር እንዲለን በምልጃሽ
ንዒ ድንግል /2/ ከልጅሽ ከአማኑኤል
አዝ . . .
የሐና የኢያቄም መልካም ተክል
የሐዋርያት ስብከት የሰማዕታት አክሊል
ነይ ድንግል /2/ ነይልን ፈጥነሽ ድንግል
አዝ . . .
አሕዛብ ነገሥታት ይገዙልሻል
የናቁሽም ሁሉ ይሰግዱልሻል
የእግዚአብሔር ከተማ /2/ ድንግል ሆይ ጽዮን ይሉሻል
አዝ . . .
በጥልቅ ማዕበል ሳለን
በኃጢአት ወጥመድ ተይዘን
ድረሽልን /2/ ከልጅሽ አንቺ አማልጅን
አዝ . . .

26. **ፍቅርኪ መፅሐፍ**
ፍቅርኪ መፅሐፍ /4/
ለዘያነብቦ /3/ ፍቅርኪ መፅሐፍ /2/ ኧኸ

ትርጉም፡- ለሚያነበው ሰው ፍቅርሽ መፅሐፍ ነው።

## 27. <u>በአልባሰ ወርቅ</u>

በአልባሰ ወርቅ /2/ ፀዓዳ ርግብ ትመስል ማርያም ድንግል /2/
ይእቲኬ ማርያም ድንግል እምደመና ቀሊል እሙ ለእግዚእ /2/

<u>ትርጉም</u>፡- ድንግል ማርያም ወርቅን ተጎናጽፋ ነጭ ርግብን ትመስላለች፡፡
እርሷም ማርያም የጌታ እናቱ ከደመና ይልቅ ፈጣን ናት፡፡

## 28. <u>ሰአሊ ለነ ቅድስት</u>

ሰአሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን /2/
እንደ ኤፍሬም እንደአባታችን ለምኝልን እመቤታችን /2/
ተስፋቸው ነሽና ለፍጥረት ዓለም
እየተመኩብሽ እስከዘለዓለም
ኃጢአታቸው ተደምስሶላቸው
በአንቺ ጸሎት ዳነች ሕይወታቸው
አዝ . . .
ስምሽም ስልጡን ነው በእግዚአብሔር መንበር
ቃል ኪዳን ገባልሽ ዓለሙን ሊምር
በአንቺ ጸሎት ይተማመናሉ
ጠዋት ማታ ቅድስት ሆይ ይላሉ
አዝ . . .
ዓለም ስትዋጋን በምኞት ስለት
ነፍሳችን ስትዝል ሲከብዳት ኃጢአት
ጨልሞብን ግራ ሲገባን
ብርሃናችን ነይ እናታችን
አዝ . . .
የልባችን ሐዘን እጅጉን ከብዶናል
ኃጢአታችን በዝቶ መቆም ተስኖናል
እንደ ኤልሳቤጥ እንደዘመድሽ
ደስ አሰኝን ይሰማ ድምጽሽ
አዝ . . .

## 29. <u>ሐዋርያት ይብልዋ</u>

ሐዋርያት ይብልዋ/2/ ለማርያም/2/
ሰላም ለኪ/4/ ይብልዋ ለማርያም/2/ ኧኸ ኧኸ ኧኸ

<u>ትርጉም</u>፡- ሐዋርያት ማርያምን ሰላም ላንቺ ይሁን ይሏታል፡፡
ያከብሯታል፣ያገኗታል ሲል ነው፡፡

**<u>መዝሙር በእንተ ልደታ ለድንግል ማርያም</u>**

**30.** **<u>ተፈፀመ ሐና በወለትኪ</u>**
**/ዲ/ን መገርሳ - ቁ.2/**

ተፈፀመ ሐና በወለትኪ /2/
ተስፋ ቅዱሳን አበውኪ
ተስፋ ቅዱሳን አበው } /2/

ተፈፀመ ሐና በልጅሽ /2/
የቅዱሳን ተስፋ ያባቶችሽ /4/ ኸኸ

የሚዘመርበት ወቅት: ግንቦት 1

**<u>መዝሙር በእንተ ስደታ ለድንግል ማርያም</u>**

**31.** **<u>አስምኪ ቦቱ</u>**
አስምኪ ቦቱ ንግሥተ ሰማያት ወምድር/2/
ተፈፀመ/5/ ማኅሌተ ፅጌ/2/ ኸኸ

<u>ትርጉም</u>:- የሰማይና የምድር ንግሥት ሆይ እነሆ የጽጌው ማኅሌት ተፈጸመ::
ውድ ልጅሽ በእቅፍሽ እንደሚያርፍ አንቺም በዚህ ማኅሌት እረፊበት::
ደስ ተሰኝበት:: በመካከሉ ተገኝ አሳርፊው::
የሚዘመርበት ወቅት: ኅዳር 6

**32.** **<u>ድንግል መከራሽን</u>**
ድንግል መከራሽን ጥቂት ላስታውሰው
በሄሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰው
አንቺ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት
እንደችግረኛ ተነሳሽ ስደት
እረ ለመሆኑ እንዴት አለቀልሽ
ስትንከራተቺ በረሀን አቋርጠሽ
ይገድሉታል ብለሽ ለልጅሽ አስበሽ
በግብጽ በረሃ መከራሽን አየሽ
መከራሽን መከራሽን አየሽ
አዝ. . .
አዛኝቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ
እንድትደርሽልኝ በመከራ ጊዜ
መከራን ያየ ሰው መቼም አይጨክንም
አትጨክኝበኝ አደራሽን ማርያም
አደራሽን አደራሽን ማርያም

አዝ . . .

አቤት የዚያን ጊዜ ያየሽው መከራ
ያለቀስሽው ልቅሶ ጭራሽ አይወራ
የአማኑኤል እናት አንቺ መከረኛ
እድሜሽን ጨረስሽው ሆነሽ ሀዘንተኛ
ሀዘንተኛ ሆነሽ ሀዘንተኛ

አዝ . . .

የሚዘመርበት ወቅት: መስከረም 26 - ኅዳር 6(ዘመነ ጽጌ)

**33. <u>የጻድቃን እመቤት</u>**
**/መሪ. ብርሃኑ ውድነህ - ቁ.3/**

የጻድቃን እመቤት የደናግል ተስፋ
ሀገር ለሀገር ዞረች አምላክን ታቅፋ
አምላክን ታቅፋ ስትዞር በበረሀ
እንባዋ ይፈሳል እንደክረምት ውኃ
እንደ ክረምት ውኃ እንባዋ
ምንም አላገኘች አይዞሽ ባይ ዘመድ
አይዞሽ ባይ ዘመዷ ወልደ አምላክ ሳለ
ውሃ ጥም ጸንቶባት አፏ ደርቆ ዋለ
መቼ ተስኖት ነው ውኃ ለእርሷ ማውረድ
አስቦ ነው እንጂ ክብሩን ለማዋረድ
ሥልጣኑን ሽሽጎ ክብሩን ያዋረደው
ከገሀነም እሳት እኛን ሊያድነን ነው።

የሚዘመርበት ወቅት: መስከረም 26 - ኅዳር 6(ዘመነ ጽጌ)

**34. <u>ምዕረ በዘባንኪ</u>**

ምዕረ በዛባንኪ ወምዕረ በገቦኪ /2/
በሀዚለ ሕፃን/2/ እፎ ደከምኪ /4/
አንዴ አንድ ጊዜ በጀርባሽ አንድ ጊዜ በጎንሽ /2/
ሕፃን በመሸከምሽ/2/ ደከምሽ/4/
የሚዘመርበት ወቅት: መስከረም 26 - ኅዳር 6(ዘመነ ጽጌ)

<u>መዝሙር በእንተ ብስራት</u>

**35. <u>ወእንዘ ትፈትል</u>**
**/ፋንቱ ወልዴ - ቁ.4/**

ወእንዘ ትፈትል/2/ ወርቀ ወሜላተ /2/ }
አስተርአያ ገብርኤል ግብተ }
ወይቤላ/2/ እስመ ረከብኪ ሞገሰ /2/ }
በኀበ እግዚአብሔር }

ትርጉም:- ሐርና ወርቅን አስማምታ ስትፈትል
በድንገት መልአኩ ገብርኤል ታያት::
በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን መወደድን
አገኝተሻል አላት::

የሚዘመርበት ወቅት: ታኅሳስ 22፣ መጋቢት 29

36. አመ ኀደረ
/ስብሐት ለሥላሴ - ቁ.1/

አመ ኀደረ ላዕሌኪ ፀሐየ ቅዱሳን ዘራማ /2/
በመንክር ግርማ/2/ ጸለለኪ /4/ ኸኸ
ሰማያዊው የቅዱሳን ፀሐይ ባደረ ጊዜ በማኅፀንሽ /2/
በሚያስደንቅ ግርማ /2/ ከለለሽ /4/ ኸኸ

የሚዘመርበት ወቅት: ታኅሳስ 22

37. አስተርአያ

አስተርአያ ገብርኤል ለማርያም/2/
ወእንዘ ትፈትል/4/ ትፈትል ወርቀ ወሜላተ/2/

ትርጉም:- ወርቅና ሐርን ስትፈትል
ገብርኤል ለማርያም ታያት::

38. ገብርኤል አብሠራ

ገብርኤል አብሠራ/4/
ለማርያም ወይቤላ ትወልዲ ወልደ/4/ ኸኸ
ትርጉም:- ድንግል ማርያምን ገብርኤል አበሰራት
ወልድንም ትወልጃለሽ አላት::

የሚዘመርበት ወቅት: ታኅሳስ 22

39. ለድንግል ገብርኤል አብሠራ

ለድንግል ገብርኤል አብሠራ /2/
ሚካኤል/2/ በክነፍ ፆራ /2/
መንጦላዕተ ደመና ሠወራ /2/ }

ትርጉም:- ድንግልን ገብርኤል አበሠራት ሚካኤል በክንፉ
ተሸከማት የደመና መጋረጃ ሰወራት/ጋረዳት/
የሚዘመርበት ወቅት: ታኅሳስ 22

**40. <u>*መልአክ በሰላም*</u>**

***/ተምሮ ማስተማር - ቁ.1/***

*መልአክ በሰላም ተናገራ መልአክ በሰላም /2/*
*ቡርክት አንቲ እምአንስት ቡርክት አንቲ /2/*
*መልአክ በሰላም ድንግልን መልአክ ተናገራት /2/*
*ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ አላት /2/*

*የሚዘመርበት ወቅት፡ ታኅሳስ 22*

<u>*መዝሙር በእንተ ዕርገታ ለድንግል ማርያም*</u>

**41. <u>*ዕርገታ ተሰምዓ*</u>**

*ዕርገታ ተሰምዓ ውስተ ሰማያት /2/*
*ወበዓታ/2/ ውስተ ገነት/4/ ኧኸ*
*ገነዘዋ ሐዋርያት/2/*
*ገነዘዋ /2/ በስብሀት/4/ ኧኸ*

*<u>ትርጉም</u>፡- ወደሰማይ ማረጓ ወደ ገነት መግባቷ ተሰማ፡፡*
*ሐዋርያት በክብር ገነዘዋት፡፡*

*የሚዘመርበት ወቅት፡ ነሐሴ 16*

**42. <u>*ወላዲተ ቃል*</u>**

**/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.2/**

*ድንግል /2/ ወላዲተ ቃል /2/*

*አሟሟትሽ በጥር ነሐሴ መቃብር - ድንግል*
*ሥጋሽ በምድር ላይ የታለ እንደፍጡር - ድንግል*
*አርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ መንበር »*

*አዝ ...*

*ሥጋሽን ሊያሳርጉ መላእክተ ሰማይ - ድንግል*
*ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ »*
*መግነዝ ተረከበ ለሐዋርያት ሊያሳይ »*

*አዝ ...*

*ትንሳኤሽን ሽተው ግራ ሲገባቸው »*
*ሐዋርያት ጾመው ተገለጥሽላቸው »*
*ተቀብራ አልቀረችም በምድር ከደጇ »*
*ወደ ላይ አረገች እሷም እንደልጇ »*

*አዝ ...*

*ለማየት ሲጓጉ የድንግልን ትንሳኤ »*
*እርገቷን አወቁ በንጹሕ ሱባኤ »*
*እኛም እንፀልይ ደጃችን እንዝጋ »*

ከወላዲተ አምላክ እንድናገኝ ዋጋ »
አዝ ...

የሚዘመርበት ወቅት: ከነሐሴ 1-16

**<u>መዝሙር ዘዘወትር</u>**

**43. <u>በስመ ሥላሴ</u>**
**/ፋንቱ ወልዴ - ቁ.4/**

ኃይልየ ሥላሴ ወጸወንየ ሥላሴ/2/
እኸ በስመ ሥላሴ /2/ እቀጠቅጥ ከይሴ/2/

<u>ትርጉም</u>:- ሥላሴ ኃይሌና መጠጊያዬ ናቸው።
በሥላሴ ስም እባቡን/ዲያብሎስን/ እቀጠቅጣለሁ።

**44. <u>የሥላሴን መንበር</u>**

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሐል ሚካኤልን ከፊት
አእላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት /2/

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት
ካህናተ ሰማይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ
ይህን ልዩ ክብር ሊያዩ የታደሉ
በጽድቅ ሥራቸው ደምቀው ይታያሉ /2/
አዝ . . .
የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሀገር
ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር
ጽድቅና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ
እግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ /3/
አዝ . . .

**45. <u>ቅዱስ ቅዱስ</u>**
**/ማ/ሰላም - ቁ.2/**

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር /2/
ዘበተዋሕዶ/2/ ይሴለስ /2/

<u>ትርጉም</u>:- በአንድነት ሦስት፣ በሦስትነት አንድ
የሚሆን እግዚአብሔር ምስጉን ጽኑዕ ልዩ ነው።

**46. <u>ስብሐት ለሥላሴ</u>**
**/ስብሐት ለሥላሴ - ቁ.1/**

ስብሐት ለሥላሴ ለፈጣሬ ኵሉ ዓለም /2/
በመላእክቲሁ ስቡህ ዘለዓለም
በመላእክቲሁ እኩት ዘለዓለም /2/ }

ምስጋና ለሥላሴ ለዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ /2/
በመላእክቱ ነውና ሲመሰገን ነዋሪ /4/

**47. <u>እናመስግነው</u>**
**/ማ/ሰላም - ቁ.2/**

እናመስግነው /2/ ጌታችንን እንደቅዱስ ዳዊት/2/
መንፈስ ቅዱስ ይቃኘን/2/ ያስተምረን/3/ እኸ
አምላካችን እንደቅዱስ ዳዊት/2/
እናመስግነው /2/ ጌታችንን እንደአባቶቻችን/2/
እኸ እናመስግነው/2/ ጌታችንን እንደቅዱስ ያሬድ/2/
<u>ስቃፊጽ ፐባጽ ያነቿቃሐ2ሐ ዴጽፅጋጺቃሐ3ሐ</u>
አምላካችን እንደአባቶቻችን/2/

**48. <u>መዓትህን አርቅ</u>**
**/ተምሮ ማስተማር ሰ/ት/ቤት - ቁ.1/**

መዓትህን አርቅ /2/ ከእኛ
ምሕረትህን አውርድ /3/ ሰማያዊው ዳኛ
ኢየሱስ ክርስቶስ /2/ ንጉሠ ራማ
በጨነቀን ጊዜ በቸገረን ጊዜ በፈተና ጊዜ ጸሎታችንን ስማ

ንጉሠ ራማ፡- ሰው መርምሮ ሊደርስበት በማይችል
ልዕልና የምትኖር ልዑል ከፍ ያልህ ንጉሥ ማለት ነው፡፡
ራማ ማለት ከፍታ ነውና፡፡ መልክአ ሚካኤል ተመልከት፡፡

**49. <u>ወመኑ መሐሪ</u>**
**/ጎልጎታ - ቁ.1/**
ወመኑ መሐሪ ዘከማከ/2/
ወኵሉ ይሴፎ ኪያከ /4/
<u>ትርጉም</u>፡- ሁሉም አንተን ተስፋ ያደርጋልና፡፡
እንዳንተ ይቅር ባይ ማነው

የሚዘመርበት ወቅት፡ በወርኃ ጥቅምት

## 50. <u>ኦ አንትሙ</u>
**/መም. ዕንቈ ባሕርይ/**

ኦ አንትሙ ሕዝበ ክርስቲያን
በከመ ተጋባዕክሙ በዛቲ ዕለት
ከማሁ ያስተጋብዕክሙ በደብረ ጽዮን ቅድስት
ወበኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም /2/ አግዓዚት

<u>ትርጉም</u>፡- እናንት የክርስቲያን ወገኖች ሆይ በዚህች ዕለት
እንደተሰበሰባችሁ ቅድስት በምትሆን በደብረ ጽዮን ነፃ
በምታወጣ በኢየሩሳሌም ይሰብስባችሁ።

## 51. <u>ሃሌ ሉያ</u>
**/አዳነች አስፋው - ቁ.2/**

ሃሌ ሉያ ለእርሱ እንዘምር በእልልታ
ክብር ይገባዋል የሠራዊት ጌታ /4/
ጸናጽል ከበሮ በገናም ይደርደር
ነፃ ላደረገን ከባርነት ቀንበር /4/
ለፍቅር ለሰላም ለምሕረት አባት
ይጎሰም ነጋሪት ይነፋ መለከት /4/
ሁሉ በእጁ ሳለ ድሃ ለሆነልን
የነገሥታት ንጉሥ ጌታችን ይመስገን /4/
ለገዛልን ርስት በደሙ ለዋጀን
በመስቀል ተሰቅሎ በሞቱ ላዳነን /4/
ስለኛ ደህንነት ሐፍረትን ለናቀው
ለአማልክት አምላክ ምስጋና ይድረሰው /4/
እኛ ክርስቲያኖች ሁላችንም ዛሬ
ለዓለም መድኃኒት እናቀርብ ዝማሬ /4/
ሃሌ ሉያ ለእርሱ እንዘምር በእልልታ
ክብር ይገባዋል ለሠራዊት ጌታ /4/
ፀናፅል ከበሮ በገናም ይደርደር
ነፃ ላደረገን ከባርነት ቀንበር /4/

## 52. <u>ለአምላካችን እንዘምር</u>
**/ብዙአየሁ ተመስገን - ቁ.1/**

ለአምላካችን አንዘምር ለጌታችን እንዘምር /2/
ብዙነው ውለታው የእግዚአብሔር /2/
ወደእኛ ለመጣው ከሰማያት ወርዶ

በበረት ለተኛው ከድንግል ተወልዶ
ለሰው ልጆች ፍቅር ሰው ለሆነው ወዶ /2/
አዝ ....
እኛ ለተሰደድን ለተሰደደልን
ተጠምቆና አጥምቆ አርአያ ለሆነን
በበደልነው ሁሉ እርሱ ለካሰልን/2/
አዝ ....
በመስቀል ተሰቅሎ ፍቅሩን ለገለፀው
ዓለምን ለማዳን ደሙን ላፈሰሰው
ለቸሩ ክርስቶስ ምስጋና ይድረሰው /2/
አዝ ....
ለሐዘን ለደስታ ስለደረሰልን
በኑሮአችን ሁሉ ስለቀደመልን
በበጎ ስጦታው ፍቅሩን ላበዛልን /2/
አዝ ....
ስለቸርነቱ ብዙ አድርጎልናል
ታዲያ ለዚህ ሁሉ ምን ይከፈለዋል
ሰዎች ዝም አንበል ማመስገን ይገባል /2/
አዝ ....

**53. ኵሉ ከንቱ**
**/ዲ. መገርሳ - ቁ.2/**

ኵሉ ከንቱ ከንቱ ንብረቱ እስመ ኵሉ ኃላፊ ውእቱ /2/
መድኃኔዓለም /2/ አድኅነነ /2/ እሞተ ከንቱ /2/

ትርጉም:- ሁሉ ከንቱ ንብረቱ ሁሉ ከንቱ ነው::
ድኃኔዓለም ከከንቱ ሞት አድነን::

**54. እናመስግነው**
**/ተስፋዬ ኢዶ - ቁ.2/**

እናመስግነው /2/
አምላካችን ውለታው ብዙ ነው /2/
ከኃጢአት ቀንበር ከሞት ቤት ለይቶ
መንግሥቱን የሰጠን ከሲኦል አውጥቶ
ዘለዓለማዊ ቤት ታላቅ ሀብት ያደለኝ
መቼም የማይተወኝ ታላቅ አባት አለኝ
አዝ ....
ፍጡራን ቢንቁኝ መጎሰቆሌን አይተው
ወዳጆች ቢሸሹኝ ተስፋቢስ ነህ ብለው
እውነተኛው ረዳት አምላኬ መች ተወኝ
ሁለት እጄን ይዞ ልጄ ተነስ አለኝ
አዝ ....

ሞታችንን ሞቶ ሕይወቱን ሳደለን
ለቸሩ ክርስቶስ ምን እንከፍለዋለን
ለታላቅ ውለታው ጌታ ለዋለልን
በእልልታ እንዘምር በአንድነት ሆነን

አዝ ....

## 55. <u>ሁላችን እንፀልይ</u>
**/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.2/**

ሁላችን እንጸልይ የሃይማኖት ጸሎት/2/
<u>እንድናውቅ ምስጢሩን</u> /2/ የተዋህዶ እምነት
የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ከገባን/2/
<u>ከቶ ምንም አይኖር</u> /2/ የሚያደናግረን
የአምላክ ሰው መሆን ምስጢረ ሥጋዌ /2/
<u>ያስረዳናል በእውነት</u>/2/ የአንድነት ሕላዌ
የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ይረቃል/2/
<u>በሃይማኖት ትምህርት</u> /2/ ጐልቶ ይታወቃል

ሁላችን እንፀልይ ....

## 56. <u>ኃይሉን ያለብሰኛል</u>
**/አዳነች አስፋው - ቁ. 2/**

ኃይሉን ያለብሰኛል ቅዱሱ ጌታዬ
የዓይኖቼ ተስፋ ታማኝ ጠባቂዬ
በሰላም ወጥቼ በሰላም እገባለሁ
እግዚአብሔር ሳለልኝ ምንስ እሆናለሁ /2/

በእርሱ ደስ ይለኛል ፍቅሩን ቀምሻለሁ
በመከራዬ ቀን በእርሱ ድኛለሁ
የዘለዓለም ደስታ በእርሱ ማመኔ ነው
ዓለሙም ንብረቱም ሁሉም ኃላፊ ነው /2/

ዘመን የማይሽረው ቀን የማይለውጠው
የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ኃያል ነው
ፍቃዱን ለማድረግ አምላክ ይመራኛል
ሕጉም ለመንገዴ ብርሃን ሆኖኛል /2/

ጎብኝቶኛል አምላክ ድንቅ አድርጎልኛል
በመስቀል ስቃዩ በደሙ ገዝቶኛል
በእርሱ ደስ ይበለን እንቅረብ ከቤቱ
አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ በረከቱ /2/

ከቤትህ በረከት ስለሰጠኸኝ

መዳንን በቃልህ ስላደረግክልኝ
ላመስግንህ እንጂ ሌላ ምን እላለሁ
ከቤትህ ላልለይ ልቤን እሰጣለሁ /2/

**57. <u>የቀደመ በደላችንን</u>**
**/አዳነች አስፋው - ቁ. 2/**

የቀደመ በደላችንን /2/ አታስብብን /2/
አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን /2/
አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይሁን ይደረግልን } /2/

**58. <u>ዘይክል ኵሎ</u>**
**/መ/ል/ቅ/ማር/ሰ/ት/ቤት - ቁ.1/**

ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር
አምላከ ነዳያን ረዳኤ ምንዱባን
ንሕነ ሀቤከ /2/ ተማኅፀነ
የድሆች አለኝታ ተስፋ ላጡ ተስፋ
ሁሉንም የሚችል ደራሽ ለተገፋ
ለእኛም ድረስልን በኃጢአት ሳንጠፋ
አዝ . . . /ናዛዜ ኅዙናን/
ከገነት ሲባረር አዳም ተሳስቶ
ባለቀሰ ጊዜ ልጅነቱን አጥቶ
ትድናለህ ብለህ ያዳንከው በመስቀል
የቅዱሳን አምላክ አቤቱ ቸል አትበል
አዝ . . . /ወተስፋ ቅቡጻን/
ሕዝበ እስራኤልን ፈርኦን ሲገዛቸው
ጭንቅና መከራ እያጸናባቸው
በእነራሔል ልቅሶ ሙሴን ላክላቸው
አዝ . . . /ረዳኤ ምንዱባን/
እኛም ወገኖችህ ወደአንተ እንጮሃለን
ከጭንቅ ከመከራ እንድታደገን
ጌታ አንተ ነህና ናዛዜ ኅዙናን
አዝ . . . /ናዛዜ ኅዙናን/
አዝ . . . /ወተስፋ ቅቡጻን/

**59. <u>ወዘምሩ ለስሙ</u>**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

ወዘምሩ ለስሙ /2/ ሀቡ አኰቴተ ለስብሐቲሁ /2/
በልዎ ለእግዚአብሔር ግሩም ግብርከ /2/

ለስሙም ዘምሩ /2/ ምሥጋናን አቅርቡ ለጌትነቱ /2/
እግዚአብሔርን /2/ ሥራህ ድንቅ ነው በሉት /2/

**60. <u>ሁላችን እናቅርብ</u>**
**/ዲ/ን መገርሳ - ቁ.2/**

ሁላችን እናቅርብ ለአምላክ ምስጋና
እሱን ለማመስገን ተፈጥረናልና /2/
ዓለምን ሳስገኝ በረቂቅ ምሥጢሩ
ለእግዚአብሔር በደስታ ዘምሩ /2/
በአምላካዊ ጥበብ ሁሉን የፈጠረው
ክብሩ እንዲታወቅ እንዲመሰገን ነው /2/
ፍጥረታት በሙሉ እንደስጦታቸው
ያመሰግኑታል ውለታውን አውቀው /2/
የበረከት አምላክ እንዲባርከን
እንዘምር ሁላችን በመንፈስ ሁነን /2/
ለኃያሉ አምላክ ለሠራዊት ጌታ
በገናውይደርደር ከበሮው ይመታ/2/
ከጥፋት ለዋጀን በከበረው ደሙ
የዝማሬን መስዋዕት እናቅርብ ለስሙ/2/

**61. <u>የሕይወት እንጀራ</u>**
**/ተስፋዬ ኢዶ - ቁ.2/**

ኑ የሕይወት እንጀራ እንብላ የሕይወት እንጀራ /2/
ለዘለዓለም በቤቱ አንኖራለን

ድዉያነ ሥጋ ጸጋው የራቃችሁ
በሥጋም በነፍስም ጽድቅ የተራባችሁ
ለመዳኑ ሕይወት አምላክ ሲጠራችሁ
በፍርሐት ቅረቡ ወደ ፈጣሪያችሁ

አዝ ....

ሥጋውን ፍሪዳ አድርጎ ሰጥቶናል
ደሙን መጠጥ አድርጎ በፍቅር አድሎናል
ከዚህ ሰፊ ማዕድ ቅረቡ ይለናል
ከቅዱሳን ኅብረት ይቀላቅለናል

አዝ ....

ኑ ወደኔ ይላል የዓለሙ ሁሉ ቤዛ
ጊዜአችን አይለፍ በዋዛ ፈዛዛ
ሥጋውን ካልበላን ንስሐ ገብተን
ደሙንም ካልጠጣን ከኃጢአት ርቀን
በመጨረሻው ቀን ዕዳ አለብን

አዝ ....

**62. <u>ማን እንደ እርሱ</u>**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

ማን እንደ እርሱ እንደ እግዚአብሔር
ቸርነቱ ብዙ በሰማይ በምድር
ሞገድና ነፋስ የሚታዘዙለት
አብሕርት ቀላያት የመሰከሩለት
ኅቱም መቃብርን ሳይከፍት የተነሣ
ነፍሳትን ያዳነ ከሲዖል አበሳ
አዝ . . .
ፈዋሴ ድውያን ቸርነቱ ብዙ
የጸጋ ልብሳቸው ጽድቅን ለታረዙ
የተዋረዱትን ከፍ ከፍ የሚያደርግ
ለባልቴቷ ዳኛ ፈራጅ ለድሃ አደግ
አዝ . . .
የጠፋውን አዳም ሊፈልግ የመጣ
ከባርነት ዓለም ከጽልመት ያወጣ
ብርሃን ዘበአማን ጨለማን ያራቀ
ሰውን ከራሱ ጋር ሞቶ ያስታረቀ
አዝ . . .
በመከራ ሳሉ ሕዝቦቹን ያሰበ
ሥጋውና ደሙን ቆርሶ የመገበ
ከባቴ አበሳ ምሕረቱ የበዛ
ጌታችን እርሱ ነው ሁላችን ቤዛ
አዝ . . .

**63. <u>መንግሥቱ ዘለዓለም</u>**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

መንግሥቱ ዘለዓለም /2/
ወምኲናኑኒ ለትውልደ ትውልድ/2/

መንግሥቱ ዘለዓለማዊ ነው /2/
አገዛዙም ለልጅ ልጅ ነው /2/

**64. <u>ለአምላክ ተቀኙ</u>**
**/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.4/**

ዘምሩለት /4/ እስኪ ለአምላክ ተቀኙለት /2/
ስለክብሩ ቃኙ ሁልጊዜ አወድሱት
ለፈጠረን አምላክ ስቡህ እንበልለት
ዓለምን ፈጥሮልን እኛን እንዲደላን
ምን እንከፍለዋለን እንበል ተመስገን

አዝ ....

ምድርን በአበባ ያስጌጠልን ለእኛ
ብርሃን እንዳናጣ ፀሐይን ዳግመኛ
ውኃ እንዳንጠማ ቀላያትን ፈጥሮ
አድሎናልና እንዘምር በአንክሮ

አዝ ....

እስኪ ዘምሩለት እንደመላእክት
እንደ አርባዕቱ እንስሳ ቀንና ሌሊት
ክብርና ምስጋና ይገባዋል ለእርሱ
እንዘምር በዕልልታ ገብተን ከመቅደሱ.

**65. <u>ከሕግ እንዳንወጣ</u>**

**/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.3/**

መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉም ያነበዋል
ምዕራፍና ቁጥሩን ሁሉም ይጠቅሰዋል
በዚህ ብቻ አይበቃም ተርጓሚ ያሻዋል

እንደ ፈቃዳችን ብንተረጉመው/2/
በውጥን የሚያስቀር ስሕተቱ ብዙ ነው/2/

ከቶ በሰው ፈቃድ ትንቢት እንዳልመጣ
ይመክረናል መጽሐፍ ከሕግ እንዳንወጣ

እንጠይቅ መምህራን ያሉት በደረጃ /2/
እናንብብ መፃሕፍት ይሁኑን ማስረጃ/2/

**66. <u>ተነሱ እንዘምር</u>**

ተነሱ እንዘምር /2/
በአንድነት ሆነን በእልልታ /2/ <u>ኧኸ</u> /3/
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር /2/
ለኃያሉ ጌታ ለልዑል እግዚአብሔር

አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

አዝ . . .

አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው ብንጠራው
አልጠገብ አለን ምንኛ ጣፋጭ ነው
አቤት የአንተ ሥራ የአንተ ልዕልና
ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና

አዝ . . .

ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫህ
በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተ ነህ

በሄድንበት ሁሉ ትከተለናለህ
ከእንቅፋት ከድንጋይ ትሰውረናለህ
አዝ . . .
ስለመልካም ሥራህ አለብን ውለታ
ለማይነገረው የማዳን ስጦታህ
ተመስገን እንበልህ ከጧት እስከማታ
ሌላ ምንም የለን የምንከፍልህ ጌታ
አዝ . . .
መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ
ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን እናውራ
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር
እስከዘለዓም ለስምህ እንዘምር
አዝ . . .

**67.** **<u>ኖላዊ ትጉህ</u>**
ኖላዊ ትጉህ /2/
ሐውጸነ /2/ በምሕረት ብዙኅ፡፡ ኧኸ /4/

<u>ትርጉም</u>፡- ቸር ትጉህ ጠባቂ ሆይ በብዙ
ምሕረት ቸርነት ጎብኘን፡፡

**68.** **<u>አትልፊ በከንቱ</u>**
**/ዲ/ን ታደለ ፊጣ - ቁ.1/**

አትልፊ በከንቱ አትድከሚ ዓለም/2/
ቆርጫለሁ እኔ ከጌታ አልለይም/2/
እኔ አልገበዝም አልደለልም
ልቤ እያወቀ አምላኬን አልክድም
ዓለምን ለመምሰል እምነት አልለውጥም
በከንቱ ማባበል ከመንገዱ አልወጣም
አዝ ....
ሥጋዊ ፍላጐት አያታልለኝም
ዓለማዊ እውቀት አያስታብየኝም
እነዚህ በአንድነት ይጠፋሉ ሁሉም
የእግዚአብሔር ጽድቅ ግን ይኖራል ዘለዓለም፡፡
አዝ...
ሰውን ለማስደሰት ትዕዛዙን አልጥስም
በከንቱ ማባበል ከመንገዱ አልወጣም
ለዲያብሎስ እጄን በፍፁም አልሰጥም
ጌታ እግዚአብሔርን አላሳዝነውም
አዝ ....
ከቅዱስ እግዚአብሔር እኔ አልለይም
በምድርም በሰማይ ያለእርሱ አልኖርም
መመኪያዬ እርሱ ነው ባዝንም ብደስትም

ሕይወቴ ጌታ ነው ያለእርሱ አልኖርም፡፡
አዝ ....

69. <u>መንክር እግዚአብሔር</u>
መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ /2/
አምላከ እስራኤል ውእቱ ይሁብ ኃይለ ወጽንዓ ለሕዝቡ ኸኸ /2/

<u>ትርጉም</u>፡- እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው፡፡
(አድሮባቸው ድንቅን ይሠራል፡፡) የእስራኤል አምላክ እርሱ
ለሕዝቡ ኃይልን እና ብርታትን ይሰጣል፡፡

70. <u>ይትባረክ እግዚአብሔር</u>
ይትባረክ እግዚአብሔር
ለዘወሀበነ /2/ ሰላም ወፍቅር ኸኸ

<u>ትርጉም</u>፡- ሰላምና ፍቅር ስለሰጠን እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

ተጠ 71. <u>እግዚአብሔር ዐቢይ</u>
እግዚአብሔር ዐቢይ /2/ ወዐቢይ ኃይሉ
ወአልቦ ጐልቍ /4/ ጐልቍ ለጠበቢሁ

<u>ትርጉም</u>፡- እግዚአብሔር ታላቅ ነው፡፡ ኃይሉም ታላቅ ጽኑ ነው፡፡
ለጥበቡም ስፍር ቁጥር የለውም፡፡

72. <u>ወሥኑስ</u>
ወሥኑስ ለዘይቤ /2/ ያዕቆብ /2/
ይእቲ ሥጋ /2/ እማርያም እንተ ነሥኣ መድኅን /2/

<u>ትርጉም</u>፡- የያዕቆብ ደም ግባት (ውበት) ያላት መድኅን
ክርስቶስ ከማርያም የነሣት (የለበሣት) ሥጋ ናት፡፡

ምስጢረ ሥጋዌን ይተረጉማል

73. <u>ዘመንበሩ ዓቢይ</u>
ዘመንበሩ ዓቢይ መንበሩ ውእቱ መንበሩ ዘኪሩቤል /2/
ያቀድም አዕምሮ /2/ ሕሊና ሰብእ /2/

<u>ትርጉም</u>፡- ከፍ ባለ ዙፋኑ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ
እርሱ የሰውን ሕሊና (ሀሳብ) አስቀድሞ ያውቃል፡፡

## መዝሙር በእንተ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

**74.** **ሰማይና መሬት**
**/መሪጌታ ዮሐንስ/**

ሰማይና መሬት የማይወስኑት/2/
ሥጋን ተዋሕዶ ታየ በልደት /2/
መለኰት ከትስብእት ይለያል ለሚሉ/2/
ቃል ሥጋ ሆነ ሲል ያስረዳል ወንጌሉ /2/
ቀድሞ በነቢያት ሁሉን ያናገረ/2/
ከሰማያት ወርዶ በድንግል አደረ/2/
ሰማይና ምድር የማይወሰኑት
ሥጋን ተዋሕዶ ታየ በልደት/2/
በጌታችን ልደት ሞት ከጠፋልን/2/
በእልልታ እንግለፀው መደሰታችንን/2/
ጌታችን ሲወለድ ለዓለሙ ሁሉ/2/
እንኳን የሰው ልጆች እንስሳት ዘለሉ/2/
በኰከብ ተመርተው ሰብአሰገል ሄዱ /2/
እጣንና ከርቤ ወርቅ ይዘው ሰገዱ/2/
ሰማይና መሬት የማይወስኑት/2/
ስጋን ተዋሕዶ ታየ በልደት /2/

**75.** **አምላክ ሰው ለመሆን**
**/መ. ብርሃኑ ውድነህ - ቁ.3/**

አምላክ ሰው ለመሆን ስለአፈቀረ/2/
በነቢያት አድሮ /2/ ትንቢት አናገረ
በአዋጅ ተነግሮ ትንቢቱ ሲፈፀም /2/
አምላክ ተወለደ /2/ ከድንግል ማርያም
ከድንግል ማርያም በለበሰው ሥጋ /2/
እኛን ወገኖቹን /2/ አለበሰን ጸጋ
ነቢያት በትንቢት ጻድቃን በውዳሴ /2/
ይነጋገራሉ /2/ ከድንግለ ሙሴ
ንጽህናዋን አይቶ ነውር እንደሌለባት /2/
መልአኩ ገብርኤል /2/ ትፀንሻለሽ አላት

ድንግለ ሙሴ (የሙሴ ድንግል) እመቤታችን ናት፡፡

**76.** **ገብርኤል አወፈየኒ**
ገብርኤል አወፈየኒ ህፃነ ማርያም ድንግል/2/
ወበቤተልሔም/2/ ተወልደ አማኑኤል/2/

ትርጉም፡- ገብርኤል ሆይ የድንግል ማርያምን

ልጅ የአማኑኤልን በቤተልሔም መወለድ አብሥረኝ።

**77.** <u>**አንፈርዓፁ ሰብአሰገል**</u>
አንፈርዓፁ ሰብአ ሰገል/2/
ረኪቦሙ ሕጻነ ዘተወልደ ለነ/2/

<u>ትርጉም</u>፡- የተወለደልንን ሕጻን /ክርስቶስን/
አግኝተው ሰብአ ሰገል ዘለሉ /ሰገዱ/።

**78.** <u>**ዘነቢያት ሰበክዎ**</u>
ዘነቢያት ሰበክዎ/2/
ወአስተርዓየ ገሀደ/2/

<u>ትርጉም</u>፡- ነቢያት የሰበኩት በገሀድ /በግልጥ/ ታየ።

**79.** <u>**አንፈርዓፁ**</u>
አንፈርዓፁ ሰብአ ሰገል/2/
አምኃሆሙ አምፅኡ መድምመ

<u>ትርጉም</u>፡- ሰብአ ሰገል ዘለሉ ሰገዱ/።
የሚያስደንቅ እጅ መንሻንም አመጡ።

**80.** <u>**በኮከብ መጽኡ**</u>
በኮከብ መጹኡ ሰብአ ሰገል/2/
ኀኸ ይስግዱ ለአማኑኤል/2/

<u>ትርጉም</u>፡- ሰብአሰገል ኮከብ አየመራቸው
ለአማኑኤል ሊሰግዱ መጡ።

**81.** <u>**መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ**</u>
**/ተምሮ ማስተማር - ቁ. 1/**

መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ /2/
የሀበነ ሰላመ ጋዳ ያበውኡ ቁርባነ /2/

<u>ትርጉም</u>፡- ዓለምን ያድን ዘንድ መጣ።
ሰላምንም ይሰጠን ዘንድ።
እጅ መንሻን እንደ ቁርባን ያስገባሉ።

**82.** **<u>የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው</u>**
**/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.5/**

የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው
ማደሪያዋስ ወዴት ነው/2/

ቦታ ጉዳናዋ ከወዴት ተቃኘ
ዝናና ወሬዋ ከወዴት ተገኘ
ፈልጐ የገዛት ማነው በቀይ ወርቅ
ባሕሩን ተሻግሮ ስሟን በማወቅ

ማነው ያወረዳት ከደመና በላይ
ድምጿንስ የሰማ ከላይ ከሰማይ
እርሷን የሚጠሉ ናቸውና ከንቱ
አይቀርላቸውም ኋላ የሞትሞቱ

ሁሉን የሚያውቅ እርሱ እርሱ ያውቅላታል
ቦታ ጉዳናዋን ያሳምርላታል
በክርስቶስ ፈቃድ በምድር ላይ ታየች
እነሆ ቤት ሠራች ሰባት ዓምድ አቆመች

ጥበብ ግን እርሱ ነው መድኃኒታችን
በሥጋ ተገልጦ እኛን ያዳነን
በደሙ ፈውሶ የተወዳጀን
ለእርሱ የመረጠን ይክበር ይመስገን/2/

**83.** **<u>መጽአ ወልድ</u>**
ሃሌ ሉያ መጽአ ወልድ ውስተ ዓለም ሃሌ ሉያ ውስተ/2/
ወለብሰ ሥጋነ ሰብአ ኮነ በአርአያ ዚአነ

<u>ትርጉም</u>:- ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ዛሬም ያለ ዓለምንም
አሳልፎ የሚኖር ወልድ ወደ ዓለም መጣ:: ሥጋችንን ለበሰ::
በእኛ አርአያ ሰው ኾነ::

**84.** **<u>ዘድንግል መናሥግተ</u>**
ዘድንግል መናሥግተ ኢያርኅዎ /2/
ኢያርኅዎ ዘኪሩቤል ኢርዕዮ ኧኸ /4/

<u>ትርጉም</u>:- የእመቤታችንን የድንግልናዋን ማኅተም
አልለወጠም (አልፈታም) ኪሩቤልም አላየውም አልመረመረውም::

## መዝሙር በእንተ ጥምቀቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

**85.** **ኢየሱስ ሖረ**
ኢየሱስ ሖረ ሀገረ እሴይ/2/
ዮሐንስ አጥመቆ በማይ/2/

ትርጉም፡- ኢየሱስ ወደ እሴይ ሀገረ ጌዶ ዮሐንስም በውኃ አጠመቀው፡፡

**86.** **መድኃኒነ**
መድኃኒነ ተጠምቀ ነዋ/2/
ይእዜኒ ለሰላም ንትለዋ/2/

ትርጉም፡- መድኃኒታችን እነሆ ተጠመቀ
አሁንስ እንግዲህስ ሰላምን እንከተላት

**87.** **ይእዜኒ**
ይእዜኒ ለሰላም ንትለዋ ለሰላም/2/
እስመ ተጠምቀ ዮም/2/ መድኃኔዓለም/2/

ትርጉም፡- መድኃኔዓለም ዛሬ ተጠምቋልና
አነሆ ሰላምን እንከተላት፡፡

**88.** **መጽዐ ቃል**
መጽዐ ቃል እምደመና ዘይብል/2/
ወወጺኦ እማይ ተርኅወ ሰማይ/2/

ትርጉም፡- ቃል ከደመና መጣ፡፡ ከውኃውም
እንደሚወጣ ሰማይ ተከፈተ፡፡

**89.** **አስተርአየ**
አስተርአየ ገሀደ /2/
በለቢሰ ሥጋ ኮነነ ዘመደ /2/

ትርጉም፡- በግልጥ ታየ፡፡ ሥጋችንን
በመልበስ ዘመድ ሆነን፡፡

**90.** **ነአምን**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

ነአምን /2/ ክርስቶስሃ ነአምን መድኅነ /2/
ዘዮሐንስ አጥመቆ በዮርዳኖስ
ዘዮሐንስ አጥመቆ /2/ በዮርዳኖስ /2/ }

}

እናምናለን /2/ መድኀን ክርስቶስን /2/
እናምናለን ክርስቶስን
ዮሐንስ ያጠመቀውን በዮርዳኖስ
ዮሐንስ ያጠመቀውን በዮርዳኖስ ያጠመቀውን /2/

<u>መዝሙር በእንተ በዓለ ቃና ዘገሊላ</u>

**91. <u>እንዘ ይገብር</u>**
እንዘ ይገብር ተአምረ ወመንክረ በውስተ አሕዛብ /2/
ወለማይኒ ረሰዮ ወይነ ኸኸ /4/

<u>ትርጉም</u>:- በአሕዛብ መካከል ድንቅ ተአምርን (ምልክትን)
ሲያደርግ ውኃውን ወይን አደረገው።

<u>መዝሙር በእንተ ስቅለቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ</u>

**92. <u>የማይሞተው ሞተ</u>**
**/ኪነ ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.5/**

አ - የማይሞተው ሞተ/2/
ሄደ ቀራንዮ እየተጐተተ
ወድቆ እየተነሳ እንዲያ እየቃተተ
ሞትን ይሽረው ዘንድ የማይሞተው ሞተ/2/

እጅና እግሩን ታስሮ ሄደ አደባባይ
እየተገረፈ ታግሶ ስቃይ
አለቀሰች ቆማ ድንግል ማርያም
ተሰቅሎባት ልጇ መድኃኔዓለም

አዝ ....

በአይሁድ አደባባይ ፍርድ ተንጋደደ
ወንበዴ ተለቆ ንጹሕ በግ ታረደ
የማይሞተው ሞተ ለሰው ፍቅር ብሎ
ዋለ ቀራንዮ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ

አዝ ....

ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ሥጋውን ለመኑ
እንዲፈቅድላቸው ሄደው ከመስፍኑ
ገንዘው ቀበሩት በአዲስ መቃብር
ቅዱስ ቅዱስ ኃያል እያሉ በክብር /2/

አዝ ....

**93.** **<u>ወፀሐፈ ጲላጦስ</u>**

ወፀሐፈ ጲላጦስ መፅሐፈ ወይብል /2/
ወይብል መጽሐፉ ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ/2/

<u>ትርጉም</u>፡- ጲላጦስ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ የሚል ጽሑፍ ጻፈ፡፡

**94.** **<u>ምድረ ቀራንዮ</u>**
**/ዲ. መገርሳ በቀለ - ቁ.1/**

ተ ምድረ ቀራንዮ ምድረ ጐልጐታ /2/
መድኃኒት ክርስቶስ በአንቺ ተንገላታ
ጠ የዓለም መድኃኒት በአንቺ ተንገላታ
መስክሪ አንቺ ምድር ግዑዚቷ ስፍራ /2/
መድኃኒት ክርስቶስ ያየብሽ መከራ /2/
ደሙ እንደውሃ ሲወርድ በመስቀሉ ላይ /2/
መከራን ሲቀበል በዚያች ምድር ላይ /2/
አዝ . . .
ፀሐይ ከለከለች ከመስጠት ብርሃን /2/
ለመሸፈን ብላ የአምላካን እርቃን /2/
ሁሉን ማድረግ ሲችል ስልጣን ሲኖረው /2/
በቀራንዮ መስቀል ፍቅሩ አዋለው /2/
አዝ . . .
በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ እያለ /2/
ተገርፎ ተሰቅሎ ቀራንዮ ዋለ /2/
እጆቹና እግሮቹ በችንካር ተመተው /2/
ይቅርታን አድርጎ ለዚያ ኃጢአታቸው /2/
አዝ . . .
ቸሩ መድኃኔዓለም እባክህ ማረን /2/
ደካሞች ነንና እንዳንቀር ወድቀን /2/
በቆረስከው ሥጋ ባፈሰስከው ደም /2/
አቤቱ ተራዳን እስከ ዘለዓለም /2/
አዝ . . .

**95.** **<u>ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን</u>**
**/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.2/**

ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን አባት ሆይ በመስቀል ሆነህ አባት ሆይ
ድምጽህን በማሰማት አባት ሆይ ነፍስህን ሰጠህ አባት ሆይ
ከዋክብተ ሰማይ በሙሉ ረገፉ
ጨረቃና ፀሐይ ደምን አጎረፉ
ብርሃናት ጨለሙ ጠፍተው ተለያዩ
ሥጋህን በመስቀል ተጋልጦ ስላዩ
አዝ ....

ጌታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ
አሰምቶ ጮኸ ተጠማሁ እያለ
ማርና ወተትን ለሚመግበው
ሐሞት አመጡለት ይቅመሰው ብለው

አዝ ....

አካሉ ሲወጋ ውኃ ደም ፈሰሰ
በምድር ተረጭቶ ዓለምን ቀደሰ
የእሥራኤል ሴቶች ዋይዋይ ሲሉልህ
ለእነርሱ አዘንክ እንጂ ለአንተስ አላሰብህ

አዝ ....

እናትህ ስታለቅስ በመስቀል ሥር ሆና
ዮሐንስን ሰጠህ ጠብቆ እንዲያፅናና
መላእክትም ታዩ አጋንንትም ሸሹ
የአይሁድ ሠራዊት ፈርተው ተረበሹ

አዝ ....

## <u>መዝሙር በእንተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ</u>

**96. *<u>ምድር ፀዳች</u>***

**/ኪነጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.5/**

ምድር ፀዳች ሐሴት አረገች
ምድር ፀዳች ከእድፍ ነፃች
በክርስቶስ ደም በእውነት ታጠበች /2/

ሴቶች ትንሣኤውን ሲያወሩ በደስታ /2/
ጮኻ ስትመሰክር ምድር አፍዋን ከፍታ /2/
የተዘጋው ዓለት ሲገለባበጥ /2/
ምን ተናገሩ አይሁድ ከፍርድ ለማምለጥ
አያልቅባቸውም የእነርሱ ፈሊጥ /2/

አዝ ....

መግነዙ ተገኝ ከመቃብር ወድቆ /2/
ምልክት እንዲሆን ተወላቸው አውቆ /2/
እሑድ በማለዳ መቃብሩ መከነ /2/
ሁሉም ተለውጦ ለቅሶው ደስታሆነ /2/

አዝ ....

ሁለቱ መላእክት ብርሃን የለበሱ /2/
ተነስቷል አሏቸው ሴቶች ሲደርሱ /2/
ሐዋርያት ሰምተው ዜና ትንሳኤውን /2/
አላቸው በድንገት ሰላም ለእናንተ ይሁን /2/

አዝ ....

*መቃብሩ መከነ መቃብሩ ባዶ ሆነ ማለት ነው፡፡*

**97.** **<u>ክርስቶስ ተንስአ</u>**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ. - ቁ.1/**

*ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን በዓቢይ ኃይል ወስልጣን /2/*
*አሠሮ ለሠይጣን አግዓዞ ለአዳም*
*ሰላም /3/ እምይእዜሰ ይኩን ሰላም /2/*

*ክርስቶስ ተነሣ ከሙታን በታላቅ ኃይልና ስልጣን*
*ሰይጣንን አስሮ ነጻ አወጣው አዳምን*
*ሰላም /3/ ከእንግዲህ ሰላም ይሁን /2/*

**98.** **<u>እንዘምር ሁላችን</u>**
**/መሪጌታ ፀሐይ/**

*እንዘምር ሁላችን ለቸሩ ፈጣሪ /2/*
*በትንሣኤው ኃይሉ ሞትን አሣፋሪ /2/ ሞትን አሣፋሪ*
*እሰይ አገኘነው ሕይወታችንን /2/*
*ደስ ይበለን አዝ*
*ትጉህ የማይተኛ ጊዜውን አክብሮ/2/*
*ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል በርብሮ /2/ ከሲኦል በርብሮ*
*አዝ ....*
*አረገ በስብሐት አረገ በእልልታ /2/*
*ሞትን ድል አድርጎ የሠራዊት ጌታ /2/ የሠራዊት ጌታ*
*አዝ ....*
*ሞት ሆይ ወዴት አለ ከቶ ማሸነፍህ /2/*
*ኃይልህ ተዋረደ አንተም ድል ተመታህ /2/ አንተም ድል ተመታህ*
*አዝ ....*

**99.** **<u>በትንሣኤከ</u>**
*በትንሣኤከ እግዚኦ ተዘከረነ*
*አመ ትመጽእ በመንግሥትከ /2/*
*ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳኒከ*
*ወምስለ አዕላፍ መላእክቲከ /2/*

*<u>ትርጉም</u>፡- ከቅዱሳንህ ሁሉ ጋር ከአዕላፍ መላእትህም ጋር በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አቤቱ በትንሣኤህ አስበን፡፡*

**100.** **ሰላም ሰላም**
**/ፋንቱ ወልዴ- ቁ.5/**

ሰላም ሰላም /2/
ኧሸ እምይእዜሰ ይኩን ሰላም /2/

ሰላም ሰላም /2/
ኧሸ እንግዲህስ ይሁን ሰላም /2/

**101.** **የትንሣኤው ብርሃን**
**/መሪጌታ ፀሐይ/**

የትንሣኤው ብርሃን የሰው ልጅ ሕይወት /2/
አዳምን መለሰው ከወጣበት ቤት /2/
እሰይ የምሥራች ደስ ይበላችሁ
ሞትን ድል አድርጎ ተነሳላችሁ /2/ አዝ
ያ በሙሴ አሪት የተነገረው /2/
ሞትን ዛሬ አጥፍቶ የተነሳው ነው /2/
አዝ ....
ማርያም መግደላዊት ምንኛ ታደልሽ /2/
ከሰው ሁሉ በፊት ትንሣኤን አየሽ /2/
አዝ ....
ብርሃን ያሳየዋል የጽድቅንም ፋና /2/
ለሚገዛለቱ በእውነቱ ጎዳና /2/
አዝ ....
ስምህን ተናገርኩ ሁሉም ተቀበለ /2/
ከጥፋት ልጅ በቀር ማንም አልታጎለ /2/
አዝ ....
አምላክ ሆይ ባርከህ ቀድሳቸው /2/
ከጥፋት ልጅ በቀር ሁሉም የአንተው ናቸው /2/
አዝ ....
አንድ ይሁኑ እነርሱም በሰላም በፍቅር /2/
እኔም አንድ እንደሆንኩ ከቸሩ አባቴ ጋር /2/

**መዝሙር በእንተ ዕርገቱ ለእግዚእነ**

**102.** **ሞዖ ለሞት**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ. - ቁ.1/**

ሞዖ ለሞት እግዚኡ ለአዳም
ተንሥአ ወልድ በሣልስት ዕለት /2/
ፈፂሞ ሥርዓተ አርቲዖ

ሃይማኖተ ዐርገ ኀበ አቡሁ /2/

የአዳም ጌታው ወልድ ሞትን
አሸንፎ በሶስተኛው ዕለት ተነሳ /2/
ሃይማኖትን አቅንቶ ሥርዓትን
ፈጽሞ ዐረገ ወደአባቱ /2/

**103. <u>ይቤሎሙ ኢየሱስ</u>**
ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ኢየሱስ ይቤሎሙ /2/
ሰማይ አዓርግ ኀበ አቡየ ወአቡክሙ /2/

<u>ትርጉም</u>:- ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ
ሰማይ ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ አርጋለሁ አላቸው::

**104. <u>ንግበር በዓለ</u>**
<u>ንግበር በዓለ በትፍሥሕት ዮም</u> /2/
እስመ ተንስአ እግዚእነ እሙታን /2/
ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት
ዘይሴብሕዎ ሊቃነ መላእክት /2/

<u>ትርጉም</u>:- ዛሬ በደስታ በዓልን እናድርግ ጌታችን ከሙታን ተነሥቷልና::
የመላእክት አለቆች የሚያመሰግኑት እርሱ በቅዳሴ በክብር ወደሰማያት ዐረገ::

<u>መዝሙር በእንተ በዓለ ደብረ ታቦር</u>

**105. <u>የታቦር ተራራ</u>**
የታቦር ተራራ /2/ የአርሞንኤም /2/
ተደሰቱ ዛሬ በአንተ ስም ኸኸ /2/

የሚዘመርበት ወቅት: ነሐሴ 13

**106. <u>አሐደ ለከ</u>**
አሐደ ለከ ወአሐደ ለሙሴ /2/
ወአሐደ ለኤልያስ ንግበር ማኅደረ/2/ ኸኸ

<u>ትርጉም</u>:- አንድ ለአንተ አንድ ለሙሴ አንድ ለኤልያስ ቤት እንሥራ::

የሚዘመርበት ወቅት: ነሐሴ 13

## መዝሙር በእንተ ቅዱሳን መላእክት

**107.** **ሚካኤል ብሂል**

ሚካኤል ብሂል እፁብ ነገር
ገብርኤል ብሂል ወልደ እግዚአብሔር /2/
በዲበ ርእሱኒ /5/ አክሊለ ትዕምርተ መስቀል

ትርጉም፡- ሚካኤል ማለተ እፁብ ነገር ማለት ነው፡፡
ገብርኤል ማለትም የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ነው፡፡
በራሱም ላይ የመስቀል ምልክት ያለው አክሊል ተቀዳጅቷል፡፡

**108.** **ውእቱ ሚካኤል**

ውእቱ ሚካኤል ውእቱ መልአከ ኃይል /2/
ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር
ይስአል ለነ ይስአል ለኢትዮጵያ
ረዳኤ ይኩና አመ ምንዳቤ /2/

ትርጉም፡- የሰላም መልአክ ኃይልን የሚያደረግ መልአክ ሚካኤል
መንበሩ ልዑል ነው፡፡ ለእኛ ይለምንልን፡፡
ለኢትዩጵያም ይለምንላት፡፡ በመከራ ጊዜም ረዳት ይሁናት፡፡

**109.** **አንስዕ ኃይለከ**

**/መ/ል/ቅ/ማር/ሰ/ት/ቤት - ቁ.1/**

አንስዕ ኃይለከ ወንአ አድኅነነ /2/
ሚካኤል /2/ ርድአነ
ሚካኤል /2/ በጸሎትከ ተማኅፀነ /2/

ኃይልህን አንሳ መጥተህ አድነን /2/
ሚካኤል /2/ ተራዳን
ሚካኤል /2/ በጸሎትህ ለምንማፀን /2/

**110.** **ሚካኤል**

**/ማ.ቅዱሳን - ቁ.6/**

ሚካኤል እመላእክት መኑ ከማከ ልዑል/2/
አስተምሕር ለነ ሰአልናከ
በአሠርቱ ወአርባዕቱ ትንብልናከ /2/
አዝ ....
ዐይኑ ዘርግብ ልብሱ ዘመብረቅ

ሐመልማለ ወርቅ /2/
አዝ ....
ይሰግድ በብረኪሁ እስከ
ይመጽእ ሥርየት ለኃጥአን /2/ /
አዝ ....
ሚካኤል እመላእክት መኑ ከማከ ክቡር
ሚካኤል እመላእክት መኑ ከማከ ልዑል

መኑ ከማከ ክቡር መኑ ከማከ ልዑል/2/

ሚካኤል ከመላእክት እንዳንተ ያለ ማነው የአምላክ ባለሟል/2/
ለምንልን/2/ ለመንህ
በአሥራ አራቱ የጸሎት ሥርዓትህ /2/
አዝ ....
ዐይኑ የርግብ ነው የወርቅ ሐመልማል
ልብሱ የመብረቅ ነው/2/
አዝ ....
ይሰግዳል በጉልበቶቹ ለኃጥአን
እስኪሰጥ የአምላክ ሥርየቱ/2/
አዝ ....
ሚካኤል ከመላእክት እንዳንተ ያለ ማነው የአምላክ ባለሟል/2/

እንዳንተ ያለ ማን አለ/2/

**111.** **<u>ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ</u>**
**/ሊቀ ጉባዔ ታረቀኝ - ቁ.1/**

ሚካኤል <u>ሐመልማለ ወርቅ</u> /2/ ልብሱ ዘመብረቅ
ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ የወርቅ ልምላሜ
የወርቅ ልምላሜ ና ና ና ስለምንህ ቆሜ
አዝ . . . ሚካኤል

ገብርኤል <u>ሊቀመላእክት</u> /2/
ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት
በሠለስቱ ደቂቅ ናቡከደነፆር ተቆጣ
እሳቱ ነደደ ነበልባሉ ወጣ
ግን ኃያል ገብርኤል ሊያድናቸው መጣ
አዝ . . . ገብርኤል
ሠለስቱ ደቂቅ ይባርክዎ ለእግዚአብሔር
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ብለው
ምስጋና አቀረቡ ከእሳቱ ላይ ሆነው
አዝ . . . ገብርኤል

ራጉኤል ሊቀመላእክት /2/
እምህበ ላዕል ወረደ /2/
    መጋቤ ብርሃናት አንሶሳዊ ፋና
    ራጉኤል ና ና
    ና ና ና አማላጅ ነህና
አዝ . . . ራጉኤል

ኡራኤል ሊቀመላእክት /2/
ለዕዝራ ያጠጣህ ጽዋአ ሕይወት
    በዓለም ፈተና በስቃይ ኩነኔ
    ስባዝን ስጨነቅ ስጠበብ ወይ እኔ
    ኡራኤል የእኔ ኃይል ቁምልኝ ከጎኔ
አዝ . . . ኡራኤል

**112. <u>ሠለስቱ ደቂቅን</u>**
**/ዲ.ን መገርሳ በቀለ - ቁ.2 /**

ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት /2/
እኛንም አድነን /2/ ሊቀመላእክት
እኛንም አድነን ገብርኤል ሊቀመላእክት

ቂርቆስ ኢየሉጣን ያወጣህ ከእሳት /2/
እኛንም አድነን /2/ ሊቀመላእክት
እኛንም አድነን /2/ ገብርኤል ሊቀመላእክት

ሠለስቱ ደቂቅን ያወጣህ ከእሳት /2/
እኛንም አድነን /2/ ሊቀመላእክት
እኛንም አድነን ገብርኤል ሊቀመላእክት

**113. <u>እም እቶነ እሳት</u>**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ.መ - ቁ.1/**

እም እቶነ እሳት /2/ ዘይነድድ
አንገፈነ በሰፊሐ እድ ሊቀ መላእክት /2/ አዝ
    ታላቅ መመኪያ ነህ ለሚያምኑብህ ሁሉ
    ናዛዜ ኀዙናን /2/ ገብርኤል ለልዑል መልአከ ኃይሉ
የነበልባል ኃይሉ ሞገዱ ሲበዛ
ለሠለስቱ ደቂቅ የሆንካቸው ቤዛ
    አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)
ፈጥነህ የምትደርስ በዕለተ ጻሕቅ
ምስጉን ነህ አንተ ከፍ ያልክ በጽድቅ
    አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)
ዜናዊ ፍስሐ ለሰው ልጅ ድህነት
የሰላም መልአክ ነህ ሊቀ መላእክት

አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)
በአማላጅነትህ እንኮራለን
እኛ ክርስቲያኖች ደቂቀ ጽዮን
አዝ .... (ታላቅ መመኪያ ነህ)

የግእዙ ትርጉም:- ከሚነደው የእሳት ነበልባል የመላእክት
አለቃ እጆቹን ዘርግቶ አተረፈን::

በዕለተ ጻሕቅ:- በጭንቅ ቀን

114. ንቁም በበህላዌነ
/ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት - ቁ.2/
ንቁም በበህላዌነ /2/
እስከ ንረክቦ ለአምላክነ /2/ ኧኸ . . . አዝ
እስከ ንረክቦ ለአምላክነ /2/

ጌታችንን እስክናውቀው በልዕልና
ባለንበት እንጽና
አዝ . . .
ይህን ብለህ መላእክትን እንዳረጋጋህ
ቅዱስ ገብርኤል አጽናን በምልጃህ
አዝ . . .
አጠንክረን በሀይማኖት በምግባርም
ከክህደት ጥርጥር አውጣን
አዝ . . .
ቁሙ በለን በሀይማኖት ለዘወትር
እንድንበቃ ለክብር
አዝ . . .
ቅዱስ ገብርኤል አረጋጊ አጽናኝ መልአክ
መላእክትን በሰማያት እንጽና ያልክ
ከሀይማኖት ልንወጣ ስንባዝን
ና እና ባርከን ቅዱስ ገብርኤል ሆይ አጽናን
አዝ . . .

115. ከመ ትባርከነ
ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ/2/
ተዋነይ በጽድቅ/4/ ገብርኤል ሐመልማለ ወርቅ/2/

ትርጉም:- በክቡር መስቀልህ ትባርከን ዘንድ
ገብርኤል ሆይ በእውነት በረድኤት ተመላለስ::

116. ስዩም በዲበ ኃይላት
ስዩም በዲበ ኃይላት ሩፋኤል ሊቀመላእክት /2/
በዲበ ኃይላት /4/

ሩፋኤል ሊቀመላእክት /2/

<u>ትርጉም</u>:- በኃያላን መላአክት ላይ
የተሾመ የመላእክት አለቃ ሩፋኤል ነው::

**117. <u>ብቃት ስለሌለህ</u>**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

ብቃት ስለሌለህ ባትችል ልታያቸው
ብቻህን የተጣልክ ሰዎች ቢመስላቸው
ከአንተ ጋራ ያሉት እጅግ ብዙ ናቸው
ድካም ብቸኝነት የሶርያ ጭፍራ
ችግር ሰይፉን መዞ ከቦ ሲያስፈራራ
አለቀልኝ ብለህ ልቤ ሆይ አትፍራ
ቅዱሳን መላእክት አሉ ከአንተ ጋራ
አዝ . . .
ተሰደህ ብትሄድ በባቢሎን ማዶ
ኑሮህ ሬት ሲሆን ማዕረግህ ተዋርዶ
በዕንባ ብትዋጥም ጽዮንን እያሰብህ
በዙሪያህ ሰፍረዋል መላእክት ሊያጽናኑህ
አዝ . . .
ዓለም ኢያሪኮ ሰባት ግንብ አጥራ
ኃጢአት ስታደባ ቀስቶቿን ወጥራ
የተሸነፍክና ያለቀ ሲመስልህ
የእግዚአብሔር ሠራዊት በዙሪያህ አሉልህ
አዝ . . .

<u>መዝሙር በእንተ ቅዱሳን</u>

**118. <u>ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ</u>**
**/ዓምደ ሃይማኖት ሰ/ት/ቤት - ቁ.2/**

ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ
በአካለ ሥጋና በአካለ ነፍስ /2/ ያሉ
ከፈጣሪ አማልደው እኛን ያስምራሉ

የእግዚአብሔር ዐይኖቹ ጻድቃንን ከማየት
ጆሮዎቹም አይርቁም እነርሱን ከመስማት
የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይልን ታደርጋለች
በምልጃቸው እንመን አናመንታ በአንዳች
አዝ . . .

ጊዜያዊው ፈተና ሳያስቅቃቸው
እሳትና ስለት ሳያስፈራራቸው
ሰማያዊው ተስፋ ስለሚታያቸው
በመከራ/በፈተና ሁሉ ጸኑ በእምነታቸው

አዝ . . .

ኃጥኡ ነዌ እንኳን በሲዖል እያለ
ስለወንድሞቹ ምሕረት ከለመነ
እናንተማ ጻድቃን በገነት ያላችሁ
ምንኛ ትረዱን አምነን ስንጠራችሁ

አዝ . . .

ቀዝቃዛ ውኃ እንኳን በጻድቅ ሰው ስም
የሚያጠጣ ቢኖር ዋጋው አይጠፋም
ብሎ እንዳስተማረን ጌታ በወንጌል
አምነን እንፈጽመው ዋጋ ያሰጣል

አዝ . . .

## 119. <u>*ለምኑልን*</u>

**/ተምሮ ማስተማር - ቁ.1/**

ቅዱሳን ሰማዕታት ጻድቃን
ለምኑልን ለኛ ምሕረትን
ግሩማን መላእክት ለዓይን

ሚካኤል ገብርኤል ሱራፌል ኪሩቤል
ካህናተ ሰማይ ዑራኤል ሩፋኤል
ሱርያኤል ፋኑኤል አፍኒን ራጉኤል
ቅርናኤል ናትናኤል ሱራኤል ፍናኤል

አዝ ....

ለእስራኤል ነቢያት ሕዝቅኤል ዳንኤል
ዳዊት ሰሎሞን ኤርሚያስ ሳሙኤል
ኢሳይያስ አሞፅ ሐጌ ዘካርያስ
ዕንባቆም አብድዩድ ናሆም ሶፎንያስ

አዝ ....

ጴጥሮስ ጳውሎስ ሐዋርያት
የተሰዋችሁ ለተዋሕዶ እምነት

አዝ ....

እስጢፋኖስ ዲያቆን ቅዱስ ጊዮርጊስ
መጥምቁ ዮሐንስ መርቆሬዎስ

አዝ ....

ተክለሃይማኖት ዜና ማርቆስ
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ

አዝ ....

ጻድቃን ሰማእታት ቅዱሳን መላእክት
ምሕረት ለምኑላት ሆናችሁ በአንድነት

አምላክ ተለመናት ኢትዮጵያን
እጆችዋን ዘርግታ ስትማፀን
አዝ ....

**120. <u>ወጽአ እምድረ ካራን</u>**
ወጽአ እምድረ ካራን ወቦአ ብሔረ ከነዓን /2/
ተአመነ አብርሃም /2/ በእግዚአብሔር:: /2/

<u>ትርጉም</u>:- ከካራን ምድር ወጥቶ ወደ ከነዓን ሀገር ገባ::
አብርሃም በእግዚአብሔር ታመነ::

**121. <u>በጾም ወበጸሎት</u>**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ. - ቁ.1/**

ሃሌ ሃሌ ሉያ በጾም ወበጸሎት
ተመጠወ ሙሴ ኦሪተ አሥሩ ቃላተ /2/
ተመጠወ ሙሴ ጽላተ አሥሮነ ቃላተ

ሃሌ ሃሌ ሉያ በጾምና በጸሎት
ተቀበለ ሙሴ ኦሪትን አሠርቱ ቃላትን /2/
ተቀበለ ሙሴ ጽላትን አሠርቱ ቃላትን

**122. <u>ካሕን ወነቢይ</u>**
**/ፋንቱ ወልዴ - ቁ.4/**

በመንፈስ የሐውር እምኃይል ውስተ ኃይል/2/
ካህን/2/ ወነቢይ ካህን ወነቢይ ዮሐንስ መጥምቅ/2/

<u>ትርጉም</u>:- ካህንና ነቢይ የሆነው መጥምቁ ዮሐንስ
በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ከኃይል ወደ ኃይል ይጓዛል::
በጸጋ መንፈሳዊ ሀብት ዕለት ዕለት እየጨመረ እያደገ ይሄዳል::

**123. <u>ሐዋርያት ተባበሩ</u>**
**/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ. 4/**

ሐዋርያት ተባበሩ
በአዲስ ቋንቋ እየተናገሩ ቃሉን አስተማሩ

ከዐረገ በኋላ በአሥረኛው ቀን
ወደ ዓለም ላከው ጰራቅሊጦስን
በዝግ ቤት ውስጥ ቆዩ ቀኑን ሲጠብቁ
የተሰጣቸውን ተስፋውን እስኪያውቁ
አዝ ....
ቀኑም ደረሰና ሃምሣኛው ዕለት

ተሰብስበው ሳሉ በአንድነት ጸሎት
መንፈስ ቅዱስ ታየ በነደ እሳት
አዝ ....
ያ የተነገረው ያ የተስፋ ቃል
ወረደ ከሰማይ በእሳት አምሳል
ጴጥሮስ አሳመነ ሦስት ሺ ነፍሳት
ያንጊዜ ገሊላ በሰጠው ትምህርት
አዝ ....
ከሦስት አካል አንዱ መንፈስ ቅዱስን
ልኮ አናገራቸው ሁሉን በልሳን /2/

**124. <u>ንዋይ ኅሩይ</u>**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.5/**

መልእክተ ወንጌልን በደሙ የጻፈ
ስቃዩን ታግሶ ችሎ ያሳለፈ
በረሃብ በግርፋት በግዞት አብዝቶ
በገድል በትሩፋት ጠላትን ድል ነስቶ

ንዋይ ኅሩይ ነው ለዓለም ያበራ
ሐዋርያው ጳውሎስ ለጽድቅ የተጠራ

እንቅልፉን እያጣ ሌት ተቀን ሳይታክት
የኂላውን ትቶ ተጓዘ ወደፊት
በድካም ተጠምዶ በገድል እያረሰ
ከደማስቆ እስከ ሮም ቃሉን አዳረሰ
አዝ . . .
እውነት ለመናገር ከቶ ያላፈረ
ሕዝብን ከአሕዛብ በአንድ ያስተባበረ
አምላኩ እንዳይናቅ ከልቡ የተጋ
ጸንቶ የተጓዘ ለምትበልጠው ጸጋ
አዝ . . .
በሮም አደባባይ ሰማዕት የሆነ
የተዋሕዶ አርበኛ ለአምላኩ የታመነ
በጣዕመ ስብከቱ ዓለምን አጣፍጦ
አክሊል ተቀዳጀ ሳይታክት ሮጦ
አዝ . . .

**125. <u>ኦ ፍጡነ ረድኤት</u>**
**/ማ/ሥላሴ - ቁ. 4/**

ኦ <u>ፍጡነ ረድኤት</u> /2/
የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ ሰማዕት

ሰላም ላንተ ይሁን - ፍጡነ ረድኤት
የልዳው ፀሐይ - ፍጡነ ረድኤት
በጨካኝ ንጉሥ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገልጋይ ነህ - ፍጡነ ረድኤት
ስቃይ ያልበገረህ - ፍጡነ ረድኤት
አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሰህ

አዝ . . .

ለእምነቱ ተጋዳይ - ፍጡነ ረድኤት
ታማኝ ወታደር - ፍጡነ ረድኤት
ቢነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር
ስቃይ ሲያደርሱብህ - ፍጡነ ረድኤት
በመታገስህ - ፍጡነ ረድኤት
ሲወሳ ይኖራል ዘለዓለም ስምህ

አዝ . . .

የፈጣሪውን ስም - ፍጡነ ረድኤት
ስለመሰከረ - ፍጡነ ረድኤት
ጊዮርጊስ ሰማዕት በሰይፍ ተመተረ
የስቃይ መሳሪያ - ፍጡነ ረድኤት
ያላዘናጋህ - ፍጡነ ረድኤት
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ

አዝ . . .

ለሰማው ይደንቃል - ፍጡነ ረድኤት
የአንተ ሰማዕትነት - ፍጡነ ረድኤት
ምሳሌ ይሆናል ለሁሉም ፍጥረት
ገድልህ ይናገራል - ፍጡነ ረድኤት
ክብር እንደተሰጠህ - ፍጡነ ረድኤት
ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሃይማኖት

አዝ . . .

## 126. <u>ደም ወማይ</u>

ደም ወማይ ወሓሊብ እምነ ክሳዱ ፈልፈለ/2/
<u>ሶበ ተከለለ</u> /2/ ተከለለ ጊዮርጊስ ሰማዕት

<u>ትርጉም</u>:- ሰማዕቱ ጊዩርጊስ በተከለለ ጊዜ
(አንገቱን በሰይፍ በተቆረጠ ጊዜ) ደም ውኃ ወተትም ከአንገቱ ፈለቀ።

127. **<u>ዮም ተጽህፈ</u>**
**/ስ/ት/ቤት/ማ. - ቁ.1/**

ዮም ተጽህፈ እምነገሥት ክላሴሁ
ለጊዮርጊስ በመጥባዕት /2/
ጸለየ ጊዮርጊስ ወአውዓዮሙ
በነበልባል አማን ገባሬ ኃይል /2/

ዛሬ ጊዮርጊስ በሰይፍ መከለሉ ከነገሥት ተጻፈ /2/
ጊዮርጊስ ጸለየ በነበልባል አቃጠላቸው
እውነት ነው ገባሬ ኃይል /2/

ገባሬ ኃይል ማለት ኃይልን የሚያደርግ (ተአምረኛ) ማለት ነው።

128. **<u>አርሴማ ቅድስት</u>**
አርሴማ <u>ቅድስት</u> /2/ ወሰማዕት/2/
ወሰማዕት /5/ አርሴማ ቅድስት /2/

<u>ትርጉም</u>:- ቅድስት አርሴማ ሰማዕት (ምስክር) ናት።

129. **<u>ጊዜ እረፍታ ለሶልያና</u>**
ጊዜ እረፍታ ለሶልያና ወረደ ወልድ እምዲበ ልዕልና/2/
እምዲበ ልዕልና/6/ ወረደ እምዲበ ልዕልና /2/

<u>ትርጉም</u>:- ሶልያና (እመቤታችን) ባረፈች ጊዜ
ወልድ ነፍሷን ለመቀበል ከልዕልና ወረደ።

130. **<u>ሕፃን ወእሙ</u>**
ሕፃን ወእሙ /3/
ክልኤሆሙ ፈፀሙ ገድሎሙ /2/
ሕፃን ንዑስ /3/
ዘኢፈርኃ ትእዛዘ ንጉሥ /2/

<u>ትርጉም</u>:- ሕፃን እና እናቱ (ቂርቆስ እና ኢየሉጣ) ሁለቱም ገድላቸውን ፈፀሙ።
ታናሹ ሕፃን (ቂርቆስ) የንጉሡን ትእዛዝ አልፈራም።

131. **<u>አቁረርከ ቂርቆስ</u>**
አቁረርከ ቂርቆስ ነበልባሎ ለእቶነ እሳት ምውቅ /2/
ከመ ነደ እሳት አቁረሩ/2/ አቁረሩ ሠለስቱ ደቂቅ <u>ኸኸ</u> /3/

<u>ትርጉም</u>:- ቂርቆስ ሆይ የሚያቃጥለውን የእሳቱን ነበልባል
አቀዘቀዝህ ሠለስቱ ደቂቅ ነደ እሳቱን እንዳቀዘቀዙ።

132. <u>ነፍስየ ትባርኮሙ</u>
ነፍስየ ትባርኮሙ ወታስተበፅዖሙ ነያ/2/
ተክለሃይማኖት ወጸጋ ዘአብ ወእግዚእ ኀረያ/2/

<u>ትርጉም</u>፡- ነፍሴ ታመሰግናቸዋለች ታከብራቸዋለችም፡፡
ተክለሃይማኖትን ጸጋ ዘአብን እና እግዚእ ኀረያን፡፡

133. **<u>ዜናኩ ጽድቀከ</u>**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ. - ቁ.1/**

ዜናኩ ጽድቀከ ወነገረኩ አድኅኖተከ
ከሠትኩ ቃላቲከ ለሕዝብከ ኢትዮጵያ /2/
በጸጋሁ ለመንፈስ ቅዱስ ወመሀርክዎሙ
አነ ይቤ ያሬድ ካህን /2/

ጽድቅህን ነገርኩ አዳኝነትህን አስተማርኩ
ቃላትህን ለኢትዮጵያ ሕዝብህ ገለጥኩ /2/
እኔም በመንፈስ ቅዱስ ፀጋ
አስተማርኩአቸው አለ ያሬድ ካህን /2/

134. **<u>አልቦ እምቅድሜሁ</u>**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ. - ቁ.1/**

አልቦ እምቅድሜሁ ወአልቦ እምድኅሬሁ
ማኅሌታይ ሰብእ ዘከማሁ /2/
ያሬድ ካህን ይኬልህ ትንሣኤሁ ኢያዓዱ
እንስሳ ወሰብእ እምነ ሥላስ ዜማሁ /2/

ከእርሱ በፊት ከእርሱም በኋላ
እንደእርሱ ማኅሌታይ ሰው የለም /2/
ያሬድ ካህን ትንሣኤውን ይናገራል
ሰው ወይም እንስሳ ለሦስት ዜማዎቹ አይወጣም /2/

135. **<u>ብፁዕ ውእቱ</u>**
**/ውሉደ ያሬድ ሰ/ት/ቤት - ቁ.1/**

ብፁዕ ውእቱ ዘገብረ ተዝካረከ
ወዘጸሐፈ <u>መጽሐፈ ገድልከ</u> /2/ /2/
አነ እሁቦ ሕይወተ ዘለዓለም
ወአወርሶ መንበረ ክብር
ይቤሎ እግዚአብሔር ለያሬድ ካህን /2/

ንዑድ ነው ክቡር ነው ያደረገ ተዝካርህን
የጻፈ ገድልህን ያስጻፈ ገድልህን /2/

እኔ እሰጠዋለሁ የዘለዓለም ሕይወትን
አወርሰዋለሁ መንግሥተ ሰማያትን
ብሎታል እግዚአብሔር ለያሬድ ካህን /2/

## <u>መዝሙር በእንተ ጾም</u>

**136. <u>እንፁም እንፀልይ</u>**
**/ኪነ ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.5/**

እንጹም እጸልይ/2/ ሁላችን/2/
ድኅነት እንድናገኝ ከመድኃኒታችን /2/ እንጹም ሁላችን
የሰው ልጅ እንዳትሆን የመንፈሱ ድኃ
ሰጥቶሃልና ዕድሜን ለንስሐ
አርባ ሌሊትና አርባ ቀን የጾመው
ኃጢአት ኖሮት ሳይሆን የሰው ልጅ ለአንተ ነው።
መብላት ለሥጋ እንጂ ለነፍስ አይጠቅምም
እንዳለ መጽሐፍ ሰው በእንጀራ አይኖርም
ስትጾም ስትጸልይ ለሰዎች ተመች
ፊትህን አታክፋ እንደግብዞች
መከራና ችግር ቢደራረብብህ
ሰይጣንን ድልንሳው በጾም በጸሎት
ገዳመ ቆሮንቶስ የክርስቲያን አርማ
ዝናሽ ተነገረ በዓለም ተሰማ

**137. <u>ሙሴኒ ጾመ</u>**
ሙሴኒ ጾመ /2/ በደብረ ሲና
እግዚእነ ጾመ አርአያሁ ከመ የሀበነ።

<u>ትርጉም</u>፡- ሙሴ በደብረ ሲና (በሲና ተራራ) ጾመ።
ጌታችንም ምሳሌውን (አርአያውን) ሊሰጠን ጾመ።

## <u>መዝሙረ ንስሐ</u>

**138. <u>ሥጋውና ደሙን</u>**
**/መሪጌታ ብርሃኑ ውድነህ - ቁ.3/**

ሥጋው እና ደሙን አምኖ የሚቀበል /2/
የዘለዓለም ሕይወት አግኝቶ ይኖራል /2/
የአቤልን መስዋዕት የተቀበልክ አምላክ /2/
ለእኛ ለምዕመናን መንፈስ ቅዱስን ላክ /2/
ሥጋውን የበላ ደሙንም የጠጣ /2/
በስጋም በነፍስም የለበትም ጣጣ /2/

ከኃጢአት ደዌ የሚፈውሳችሁ/2/
ሥጋው እና ደሙ ከዚህ አለላችሁ /2/

**139.** **<u>ስማኝ አምላኬ</u>**
**/አዳነች አስፋው - ቁ.2/**

አጥን ቴም ኃይሉ ደከመ
በኃጢአት ደዌ ታመመ
መከራዬን አይተህ አስበኝ
ምሕረት እኔን ያድነኝ
ነፍሴም በሃዘን ታወከች
የስቃይ እንባን ቋጠረች
እስከመቼ ዝምታ ጌታዬ
አንተ አይደለህ ወይ ተስፋዬ
በደሌም ቢበዛ ማረኝና
አገልጋይ አድርገኝ እንደገና
እንዲህ በሰይጣን ታውኬ
ችላ አትበለኝ አምላኬ
አልጋዬን በእንባ እያጠብኩኝ
ደዌዬ በዝታ አለቀስኩኝ
ጠላቴም ኃይሉን አጠንክሮ
ሊያጠፋኝ መጣ ፎክሮ
ስማኝ አምላኬ መጣሁኝ
ከመስቀልህ ሥር ወደቅኩኝ /3/

**140.** **<u>በከሃሊነቱ</u>**
**/ኪነጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.4/**

በከሃሊነቱ በአምላክነቱ /2/
ይቅር ይለናል ይታደገናል /2/ በቸርነቱ
ምን ይከፈለዋል ምን ይሆን ዋጋው
ለፈጠረን ጌታ ለይቅር ባይው
የድህነትን መንገድ ንስሐን የሠራ
እንዳንጠፋበት ነው ዳግም በመከራ
ይቅር ይለናል ይታደገናል /2/ በቸርነቱ
አዝ . . .
የሰው ልጅ ከኃጢአት እስኪመስ ድረስ
አይቸኩልም እርሱ መአትን ለማድረስ
ትዕግስቱ ሰፊ ነው ሥራው ረቂቅ
ቸርነት ገንዘቡ ቢሰጠው አያልቅ
ይቅር ይለናል ይታደገናል /2/ በቸርነቱ
አዝ . . .

## መዝሙር በእንተ መስቀሉ ለእግዚእነ

**141.** **መስቀልከ**
መስቀልከ ኸኸ ዕፀ መድኃኒት/2/
ዕፀ መድሃኒት /4/ መስቀልከ /2/

ትርጉም:- መስቀልህ የድኅነት ተክል ነው::

**142.** **በመስቀልከ**
በመስቀልከ ርድአነ /2/
ወበኃይልከ ተማህፀነ/2

ትርጉም:- በመስቀልህ እርዳን በኃይልህም ጠብቀን::

**143.** **መድኃኒት**
መድኃኒት ዕፀ ሕይወት /2/
ዝንቱ ውእቱ መስቀል ኸኸ /2/

ትርጉም:- መድኃኒት የሕይወት ተክል ይህ መስቀል ነው::

## መዝሙር በእንተ ቤተ ክርስቲያን

**144.** **የቅዱሳን በዓት**
**/ማ. ቅዱሳን - ቁ.3/**

ልቡና የሚመስጥ መዓዛ እጣኗ
ሕሊናን ይገዛል ዝማሬ ድጓዋ
የቅዱሳን በዓት የጸሎት ዋሻቸው
ቤተ ክርስቲያን ናት አምባ መጠጊያቸው } አዝ
የመላእክት ዜማ የአዕዋፍ ዝማሬ
የሚለቀምባት የትሩፋት ፍሬ
አዝ . . .
ይዘምሩባታል በአንድነት ተባብረው
የሌዋዊው በትር ፀናዕል ከበሮው
አዝ . . .
ወራዳዋን ዓለም የናቋት በቅድሚያ
የእምነት አርበኞች ያገኟት በፍልሚያ
አዝ . . .
የገድላቸው ተዓምር መንቦግቦጊያ መቅረዝ
የሰማዕታት አክሊል የሥራቸው ደሞዝ
አዝ . . .
መውደቂያዬ ይሁን ከመቃብራቸው

ይፈውሳልና ተረፈ አጽማቸው
አዝ . . .
ከኃጥአን ድንኳን መውጣቴ ነው ዛሬ
የቅዱሳን በዓት ልትሆነኝ ሀገሬ
አዝ . . .

**145.** **ተቀደሲ**
ተቀደሲ ወንሥኢ ኃይለ ኦ ቤተ እግዚአብሔር /2/
እስመ ናሁ ንጉሥኪ በጽሐ እግዚአብሔር /2/

ትርጉም:- የእግዚአብሔር ቤት ሆይ ክበሪ ከፍም በይ ኃይልንም ንሺ::
የሚያበራልሽ ንጉሥሽ እግዚአብሔር እነሆ መጥቷልና::

**146.** **እምርጉቅሰ**
**/ሰ/ት/ቤት/ማ. - ቁ.1/**

እምርጉቅሰ ርእይዋ ወተአምኀዋ
ወአእመሩ ከመ ሀገሮሙ ይእቲ /2/
ገነት ይእቲ ነቅዓ ገነት አዘቅተ
ማየ ሕይወት ማኅደር ለንጹሐን /2/

ከሩቅ ሆነው አይዋት ተሳለሚት
ሃገራቸውም እንደሆነች አወቁ /2/
ገነት ናት ነቅዓ ገነት የሕይወት
ምንጭ የንጹሐን ማደርያ /2/

በግንቦት 21 ቀንም ስለእመቤታችን ሊዘመር ይችላል::

**147.** **አይ ይእቲ**
አይ ይእቲ ዛቲ እንተ ታስተርኢ
እምርጉቅ ከመ ማኅቶተ ደብረ ገነት /2/
ሙሴኒ ርእያ ሀገር ቅድስት
ዕዝራኒ ተናገራ /3/ ዘመራ ዳዊት /2/
ትርጉም:- ያቺ እንደመብራት ከሩቅ የምትታይ
የገነት ተራራ ሙሴ ያያት ዕዝራም ትንቢት የተናገረላት
ዳዊትም የዘመረላት እንዴት ያለች (ድንቅ) ናት::

**148.** **አመ ትትሐነጽ**
አመ ትትሐነጽ ኢየሩሳሌም በዕንቈ
ሰንፔር ወበከርከዴን በዕንቈ ሰንፔር /2/
ዓረፋቲሃ ለኢየሩሳሌም ወማኅፈዲሃ
በወርቅ ልቡጥ ወመርህባሰ ለኢየሩሳሌም /2/

ትርጉም፡- ኢየሩሳሌም (ቤተ ክርስቲያን፣ መንግሥተ ሰማያት) በዕንቈ፣ በከርከዴንና በሰንፔር በታነጸች ጊዜ ግድግዳዎቿና አጥሮቿ በወርቅ የተለበጡ ናቸው።

149. **ቤተክርስቲያን አሐቲ**
ቤተክርስቲያን አሐቲ አንቀጸ
አድኅኖ ይእቲ /2/ ደብረ ምሕረት /2/
ትግሁ ባቲ/2/ ሕዝበ ክርስቲያን ኧኸ እንበለ ጽርዖ /2/

ትርጉም፡- ቤተክርስቲያን አንዲት ናት። የድህነት በርም ናት።
የምሕረት ተራራ ናት። የክርስቲያን ወገኖች ያለማስታጐል
(ያለማቋረጥ) ትጉባት (አገልግሉባት)።

## መዝሙር በእንተ ዓውደ ዓመት

150. **ዓውደ ዓመት መጽአ**
ዓውደ ዓመት መጽአ /2/
ይእዜሰ ዮሐንስ ተፈሥሐ /2/ ኧኸ

ትርጉም፡- ዓውደ ዓመት መጣ። እንግዲህስ ዮሐንስ ደስ ይበልህ።

151. **ዓውደ ዓመት ለባርኮ**
ዓውደ ዓመት ለባርኮ ባርኮ ዓውደ ዓመት /2/
ንዒ ማርያም ለምሕረት ወሣህል /2/ ኧኸ

ትርጉም፡- ዓውደ ዓመትን ለመባረክ ማርያም ሆይ ለምሕረት እና ለይቅርታ ነይ።

152. **አመ ከመ ዮም**
አመ ከመ ዮም /6/
ያብጽሐነ /3/ አመ ከመ ዮም ኧኸ /2/

ትርጉም፡- እንደዛሬው ለከርሞ ያድርሰን።

153. **ያብጽሐነ**
ያብጽሐነ አመ ከመ ዮም /2/
አመ ከመ ዮም /2/ ያብጽሐነ /2/

ትርጉም፡- እንደዛሬው ለከርሞ ያድርሰን።

**154.** **ርዕሰ ዓውደ ዓመተ**

ርዕሰ ዓውደ ዓመት ዮሐንስ ወላዴ መጥቅዕ/2/
ወአበቅቴ/5/ ወላዴ መጥቅዕ/2/

ትርጉም፡- አበቅቴን እና መጥቅዕን
የሚያስገኝ የዓውደ ዓመት ራስ ዮሐንስ ነው።

## መዝሙር በእንተ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ

**155.** **የክርስቲያን ደሴት**
**/ፋንቱ ወልዴ - ቁ.1/**

የክርስቲያን ደሴት የአበው ሃይማኖት
ሐዋርያዊት ሀገር ጥንታዊት እናት
የቅዱሳን መንደር የጸሎት ቤታችን
ኢትያጵያ አንቺ ነሽ ቅድስት ሀገራችን /2/

ትነሻለሽ ለፍርድ ወንጌሉን ይዘሽ
ለሰሎሞን አምላክ ምስክር የሆንሽ
ሠልጥነሻለና በሃይማኖት ምስጢር
ኢትዮጵያ መስክሪ የሥላሴን ክብር /2/

ከእስራኤል ቀጥለሽ አምልኮ ያለሽ
የሃይማኖት ሀገር ኢትዮጵየ አንቺ ነሽ
በወንጌሉ ብርሃን ዳግም የተወለድሽ
በሥጋ በደሙ ሕይወትሌገበየሽ /2/

ጥበብን ለማየት እሥራኤል የሄድሽ
በወንጌል ተጽፏል ቀናው እምነትሽ
አይዞሽ ኢትዮጵያ ዘርጊ እጆችሽን
ጌታ ይቀበለዋል ንጹህ አምልኮሽን /2/

ሳታይ ያመንሽ ቅደስት ኢትዮጵያ
መስቀልተሽከመሽ አብሪ በዓለም ዙሪያ
የተዋህዶን ነገር መስክሪ ለዓለም
ጉልበትሽ እኮ ነው ቸሩ መድኃኔዓለም /2/

**156.** **ኢኮነ ነግደ**

ኢኮነ ነግደ ወፈላሴ ሀገሪቶሙ /2/
ሀገሪቶሙ ለቅዱሳን ኢትዮጵያ /4/

ትርጉም፡- ስደተኛ እና መጻተኞች አይደለንም።
ኢትዮጵያ የቅዱሳን ሀገራቸው ናት።

**157. <u>ሰላም ለኪ</u>**

ሰላም ለኪ ኦ ዓባይ ሀገር ቅድስት
ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር /2/
ለምድርኪ ምድረ ገነት እምአርባዕቱ
አፋላጋት ግዮን <u>አስተየኪ</u> /2/
ግዮን ፈለገ ሕይወት ውሉድኪ /2/
ፈረዩ ፍሬ ሃይማኖት

ሰላም ለአንቺ ታላቅ ሀገር ልዩም ሀገር
ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሀገር /2/
ምድርሽ የገነት ምድርን ከአራቱ
ወንዞች ዓባይ <u>አጠጣሽ</u> /2/ /2/
ዓባይ የሕይወት ምንጭ
ልጆችሽ አፈሩ የሃይማኖት ፍሬ

ዘፍ 2 ፥ 13

<u>መዝሙር በአንተ ጉባዔ</u>

**158. <u>ናሁ ሠናይ</u>**

ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም /2/
ሶበ ይሄልዉ /2/ አኃው ኅቡረ /2/ ኧኸ

<u>ትርጉም</u>፡- እነሆ መልካም ነው እነሆ ያማረ ነው
ወንድሞች በኅብረት (በአንድነት) ቢኖሩ (ቢቀመጡ)

**159. <u>ባርክ ለዝ ጉባዔ</u>**

ባርክ ለዝ ጉባዔ /2/
ንጉሠ ስብሐት /2/ ባርክ ለዝ ጉባዔ

<u>ትርጉም</u>፡- የምስጋና ንጉሥ ሆይ ይህንን ጉባዔ ባርክ፡፡